# የምሁራኑ ልኂቃን (Intellectual elite) እስከ ዛሬ በሐበሻ ላይ የሚሰነዝሯቸው ነውረኛና መሠረተ ቢስ ዘለፋዎቻቸውና አጥጋቢ መልሶቻቸው!

ይሄ ጽሑፍ ከተጻፈ ስምንት ዓመታት አልፎታል፡፡ ለመጽሐፍ ካዘጋጀኋቸው አንዱ ነበር፡፡ የዚህን ጽሑፍ ቅንጫቢ ነፍሱን ይማረውና አንጋፋው ጋዜጠኛ ጋሽ ታደሰ በሸገር ነጋሪተ ወግ (ሬዲዮ) ይተላለፍ በነበረው "እሑድ እንደገና" በተሰኘ ዝግጅቱ አቅርቦት ነበር፡፡ ያዘጋጀሁት መጽሐፍ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ወያኔን እየፈሩ የሚያሳትምልኝ አጣሁ፡፡ ስለሆነም እናንተ ለማንበብ ያብቃቹህ እንጅ እንደ ሁኔታዎችና እንደ አስፈላጊነቱ እያየሁ አንዳንድ እያልኩ እጥልላቹሀለሁ፡፡ ጽሑፉ ደናቁርት ምሁራኖቻችን በሕዝባችን ላይ ለሰነዘሯቸው ፍጹም አግባብነት ለሌለው ዘለፋቸው ሁሉ መልስ ለመስጠት የሚሞክር በመሆኑ ይረዝም ዘንድ ግድ ብሏል፡፡ እያረፋቹህ ጨርሱት፡፡

የሆነ ነገር ታወሰኝ! እነዚህ ነውረኛ ግለሰቦች ሕዝብን ያውም የዛሬን አያድርገውና ታላቁን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲሰድቡ ሲዘልፉ ሲያዋርዱ ምኑም እንዳልተነካ ወይም እንደተመረቀ ያህል ጭጭ ያለው ሁሉ እኔ የግለሰቦቹን አስተሳሰብ ተግባራቸውን ከንቱነትና መናኛነት ለመግለጥ  እነሱን ደናቁርት በማለቴ "ይሄ ባለጌ! ተሳዳቢ! ለምን ይሳደባል?..." እያለ እንቡር የሚል መኖሩን ሳስብ እጅግ ይገርመኛል፡፡

ነሱ ሕዝብን ያህል ነገር እንዲዘልፉ እንዲሳደቡ የፈቀደ ሁሉ እኔ ግለሰቦቹን እንድሰድብ መፍቀድ አለበት ለማለት ሳይሆን አላግባብ በግልብ ዕይታ ሕዝብ ሲያዋርዱ ዝም መባላቸው በዘለፋ ላይ ዘለፋ፣ በስድብ ላይ ስድብ፣ በተሳዳቢ ላይ ተሳዳቢ እየጨመረብን እንዲሔድና የገዛ ሕዝብንና ሀገርን አላግባብ ማዋረድ መዝለፍ መስደብ እንደ ማዕረግ እንደ ክብር እንዲቆጠር ሰዎቹም እንዲበረታቱ ማድረጉን ለመመጠቆም ነው፡፡ እንግዲህ መልካም ንባብ፡-

ብዙ ጊዜ በብዙኃን መገናኛዎች በተደጋጋሚ ሲፈጸም የሚስተዋል ስሕተት አለ፡፡ ይህ ነገር ሞያየ ብለው በያዙት ባልገባቸው ግለሰቦች ከሚጽፉት መጽሐፍ ጀምረው ባገኙት አጋጣሚና መድረኮች ሁሉ በመደጋገሙና ሊያስከትል የሚችለው ያልተስተዋለ ከባድ ችግር በመኖሩ ምክንያት  አንድ ነገር መባል እንዳለበት ስለተሰማኝ ይህ ጽሑፍ ተጽፏል፡፡

እንደነዚህ ጥቂቶች ሞያዬ ብለው እንደያዙት ሁሉ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከኅብረተሰባችን የዚህ ጥሩ ያልሆነ አገላለጽ ሰለባ የሆነው ሰው ቁጥር በመቶኛ ተሰልቶ ባይታወቅም አብዛኛውን ቁጥር መያዙ ግን የሚያጠራጥር አይመስለኝም፡፡ ያለው ሁኔታ እንዲህ ለመሆኑ በአሉታዊ ጎኑ የእነኚህ ያልገባቸው ግለሰቦች አስተዋጽኦ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ነገር ግን የሰዉ በዚህ አባባል ወይም አስተሳሰብ ተጠልፎ በአቀንቃኝነት የመያዙ ነገር ተስተውሎበት ወይም የሚያስከትለው አደጋ እንደሌለ ታውቆ ነው ብየ ለማለት በጣም እቸገራለሁ፡፡ ቢበዛ ቢበዛ በጣም ጥቂት ከሚባሉት በስተቀር የተቀረው ወሬ ያጣፈጠ ወይም ደግሞ እንዲህ በማለታቸው የሚሉትን ሰው ወይም ማኅበረሰቡን ከጠሉበት ወይም

ከሚወቅሱበት ነገር በዚህ ዓይነት ወቀሳ እንዲሰማው ቁጭት እንዲያድርበትና እንዲጸጸት የገፋፉ ያነሣሡ እየመሰላቸው እነደሆነ እገምታለሁ፡፡ ነገር ግን አያያዙን ስላላወቁበት በሕዝብና በሀገር ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል እያደረሰም ይገኛል፡፡

እንደሚታወቀው የኛ ማኅበረሰብ እንደማኅበረሰብ በጥቅል ስም ሲጠራ ሀበሻ ይባላል፡፡ ቃሉ የመጣው አቢስ ከሚባለው ከቀደምት ነገሥታቶቻችን አንዱ ስም ሲሆን በሱ ስም የተነሣ በግሪኮች ወይም በዓረቦች የሱን ሰፊ የነበረ ግዛት ሕዝብ የሆነውን ሁሉ አበሻ፣ ሐበሻ ወይም ሐበሽ (የአቢስ ሕዝብ) እንደተባልን ይነገራል፡፡ ሀገሪቱንም በሱ ስም የአቢስ ሀገር ለማለት አቢሲንያ አሏት የሚባለው አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ሐበሻ ያሉን ዓረቦች ናቸው የተደባለቀ ሕዝብ ለማለት፡፡ ሴማዊያንና ኩሻዊያን ተቀላቅለው የፈጠሩት ሕዝብ ነውና ብለው ስለሚያስቡ የሚሉም አሉ፡፡ አይ ይሄም አይደለም ሐበሻ ማለት ቃሉ ግሪክኛ ሲሆን ትርጉሙም በፀሐይ የተቃጠለ የጠቆረ ፊት ማለት ነው የሚሉም አሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ሐበሻ የሚለው ስም በዚህች ሀገር የሚኖረው ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ዘር ሳይለይ መጠሪያው እንደነበር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሐበሻ እንደሌላው ማኅበረሰብ ሁሉ የራሱ መለያዎች አሉት፡፡ ከነሱም ውስጥ ባሕል ወግ ሥርዓት ታሪክ የሌሎች መገለጫዎችም ባለቤት ነው፡፡

ከላይ እንዳልኩት በብዙኃን መገናኛ፣ በመጻሕፍት፣ በወግ፣ በጨዋታ፣ በቡና ወሬ ሳይቀር ማንነታችን በእኛው ሲነገር፣ ሲመዘን፣ ሲገመገም፣ ሲገመት፣ ቆይቷል፡፡ ሐበሻ በገዛ ራሱ ልጆች ብቻ ሳይሆን በባዕዳኑም ጭምር እንደዚህ ነው እየተባለ ስሙን ለማጥፋት ሆን ብለው ባሴሩ አሳሾች “በሬን ከቆመበት ሙዳ ሥጋ እየቆረጡ በጥሬው የሚበሉ አራዊት ናቸው” ከሚለው ጀምሮ ሌሎች በርካታ ዓይነት ወሬዎች ሲወራብን ባልዋልንበት ስማችን ሲጠፋ ቆይቷል፡፡

እንደ ሕዝብ ማንነታችን መፈተሹ ችግሮች ካሉብንም ለእነዚያ ችግሮች መፍትሔ ማፈላለግ መልካምና መበረታታት ያለበት ጉዳይ ነውና በተቸት ባሉብን ነገር ላይ መተቸታችን በራሱ ችግር የለውም፡፡ ችግሩ ያለው ሐበሻን ለመመዘን የምንጠቀምባቸው መመዘኛዎች ጥልቀት ስፋት ምላትና ሚዛናዊነት መጓደል ላይ ነው፡፡ ይህ ከምን ይጀምራል በዕለት ተዕለት ኑሯችን ወይም በማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብሮቻችን ውስጥ አንድ ያልተመቸን ወይም እንደ ማኅበረሰብ ለትዝብት የሚዳርገንን ነገር ስናይ አንዳችን ለሌላኛችን በስላቅ ድምፀት የምንጠቀመው ቃል አለ “አየ ሐበሻ!” የሚል፡፡ በጣም የሚገርመኝና የሚደንቀኝ ነገር ልክ እግዚአብሔር ነውርና ነቀፋውን ሁሉ ከያለበት ሰብስቦ የሐበሻ ሀብት ይሁን ብሎ በእኛ ጫንቃ ላይ የጣለው ይመስል በየነገሩና በየአጋጣሚው ጣልቃ የማይጥመን ነገር በሰማንና ባየን ቁጥር “አየ ሐበሻ!” ማለቱ ለምን እንደሚቀናን ነው፡፡

የሚገርማቹህ በአብዛኛው ይሄንን የምንል ሰዎች ከሀገር ወጥተን የሌሎች ሀገሮች ማኅበረሰቦችን ባሕል ታሪክና ማኅበራዊ ሕይወት ድክመትና ጥንካሬ ዐይተን ታዝበንና መርምረን ሐበሻን በሌሎቹ ዐይን እያየን ወይም እየመዘን ስለሆነ

ነው ሊባል አይደለም የሚበዛው ሰው ከተወለደበት ቀየ እንኳን ወጥቶ የሚያውቅ አይደለም፡፡ እንግዲህ አስቡት ነገሮችን ለንጽጽር የሚያቀርቡ ሰዎች ቢያንስ በሌላ በኩል ስላለው ጉዳይ በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸው የተገባ በነበረ፡፡ አንድ ሰው ይሄንን ሳያደርግ በአንድ በኩል ብቻ ያለውን ቁንጽል ግንዛቤ ይዞ "አየ ሐበሻ!" ቢል ይህ አባባሉ ከግልብ ስሜታዊነት ወይም ካለመብሰል የሚዘል ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ችግር በዚህ ብቻ አያቆምም የሌለና ልቦለድ ምናባዊ ምሳሌ ፈጥሮ ማኅበረሰቡን እስከማሸማቀቅ ድረስም ይዘልቃል እንጅ፡፡

ከእነኝህ የፈጠራ ምናባዊ ምሳሌዎች ውስጥ አንድ ሰባኪ ጸሐፊም ነኝ ብሎ መጻሕፍትን ጽፏል በተደጋጋሚ ሲላቸው የምሰማውን ሌሎቹም ጥሩ የሠሩ መስሏቸው ከሱ ተቀብለው የሚያራግቡትን አባባል ብጠቅስ፡- "እግዚአብሔር ነው አለ ኢትዮጵያዊና የሌሎች ሀገሮች ዜጎችም ባሉበት ተገለጸላቸውና ምን እንዳደርግላቹህ ትሻላቹህ? የፈለጋቹህትን ጠይቁኝ አደርግላቹሀለሁ፡፡ ነገር ግን ጠይቃቹህኝ ለእናንተ የማደርገውን እጥፍ ያህል ለየጎረቤቶቻቹህ ደግሞ አደርግላቸዋለሁ ብሎ አበሰራቸው፡፡ እናም ከኢትዮጵያዊው ውጭ ያሉት መልካም መልካም ነገርን እየጠየቁና እየተሰጣቸው ሲሔዱ ኢትዮጵያዊው ግን ሲያስበው ለሱ የሚደረግለትን እጥፍ ለጎረቤቱ የሚደረግለት መሆኑ ታስቦት ከምቀኛነቱ የተነሣ ይሄ እንዲሆን ባለመፈለጉ እግዚአብሔርን ምን እንዲያደርግለት ይጠይቃል? አንድ ዐይኑን እንዲያጠፋለት ጠየቀ ለምን ቢባል የጎረቤቱ ሁለት ዐይኖች እንዲጠፉ"

ይሄ አንደኛው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ "በሲዖል ውስጥ ነው አለ የእያንዳንዱ ሀገር ዜጋ ለየራሱ ጉድጓድ አለው ከጉድጓዱም እንዳይወጡ የሁሉም ሀገር ዜጎች ጠባቂዎች ሲኖራቸው እግዚአብሔር ለኢትዮጵያኑን ጉድጓድ ግን ጠባቂ አላስቀመጠም፡፡ ይሄንን ያደረገው ለእኛ አዝኖንል ሳይሆን ኢትዮጵያዊያን እርስ በእርሳቸው ስለ ሚመቀኛኙ አንዱ ሊወጣ ሲሞክር ሌላኛው ስለሚጎትተው ከእነሱ አንድም ሰው መውጣት ስለማይችል ጠባቂ አያስፈልጋቸውም እርስ በእርሳቸው ይጠባበቃሉ አለ" የሚሉና ሌሎች ተመሳሳይ የፈጠራ ምናባዊ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የሚገርመው ምናባዊ ፈጠራዎቹ መፈጠራቸው አይደለም ነገር ግን በተለይ የመጀመሪያው ከክርስቲያናዊ አመክንዮ (ሎጂክ) አንጻር ሲታይ ብላሽና ያልበሰለ መሆኑ እንጅ፡፡ ምሳሌው ከተመሰለም ከክርስቲያናዊ አስተምህሮ አንጻር ቢደረስ ምን አለ? በጣም የሚገርመኝ ደግሞ እነኝህን ተረቶች "እንዲህ ዓይነት ክፉዎች እኮነን!" በሚል ቁጭት ሥነምግባርና ግብረገባዊ በሆነ ሰው ስሜት እያጣፈጡ ከሚገልጹት ሰዎች ውስጥ ለምሳሌ እኔ ማንነቱን በቅርብ የማውቀው ሰው ሰብእና ብነግራቹህ በምሳሌ የገለጻቸውን ዓይነት ሰዎች እኩይ ምቀኛ መሆኑ ነው፡፡

አንድ ሌላም የሚገርመኝ አባባል አለ "ኢትዮጵያዊያን አብረው መብላት እንጅ አብረው መሥራት አይችሉም" የሚል ስለ እውነት ውሸትነቱ ወደ ኋላ እናየዋለን፡፡ በእኔ እምነት እነኝህን ምናባዊ የፈጠራ ተረቶች አባባሎች ኢትዮጵያዊ

ይፈጥራቸዋል ብየ ለማመን በጣም እቸገራለሁ፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያዊ ሆኖ እያለ የገዛ ሕዝቡን ሞራል (ቅስም) ለማነካከት ተጨንቆና ተጠቦ እነኝህን ዓይነቶች ምናባዊ ተረቶች የሚፈጥር ሰው የሚኖር ስለማይመስለኝ፡፡ ነገር ግን ከሆነ ቦታ በእኛ ላይ የሥነ ልቡና ጥቃት መፈጸም የፈለጉ ባዕዳን እየፈጠሩት እንደዚህ ላለ ሰባኪ ነኝ ጸሐፊም ነኝ ለሚል ወገናችን ከሕዝብ ጋር ቀጥተኛ ግልኙነት ላለው የእኛ ሰው የሚያቀብሉት ይመስለኛል፡፡ እሱም በየዋህነት ካለሙብሰል የሚፈጥረውንና የሚያመጣውን ኪሳራ ሳያውቅ ሳያጤን የሚያናፍሰው ይመስለኛል፡፡ በተለይ ደግሞ ጉዳቱን የከፉ የሚያደርገው ነገሩ የብዙኃን መገናኛውን ሽፋን አግኝቶ ሲነዛ ነው፡፡ ምክንያቱም የኛ ማኅበረሰብ በብዙኃን መገናኛዎች የተነገረውን ነገር ሁሉ እውነት አድርጎ የሚቆጥር በመሆኑ ሊፈጥር የሚችለው ችግር ቀላል አይሆንም፡፡

በዚህ አጋጣሚ እዚህ ላይ ለብዙኃን መገናኛ ሰዎች ላሳስብ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር በተለይ እንዲህ ዓይነት ከባድና በማኅበረሰብ ሥነልቡና ላይ ያነጣጠረ ትችትም ሆነ ነቀፋ እየተቀባበሉ ከማናፈሳቸው በፊት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ስለ ትክክለኛነቱ፣ በቅጡ የተጤነ ስለመሆኑ፣ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ስላለመኖሩ፣ አባባሉ ማኅበረሰቡን ወይም የሚበዛውን ክፍል ሊወክል ሊገልጽ ስለመቻሉ ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ ምክንያቱም አንድን ማኅበረሰብ ማንነቱን ሥነልቡናዊ ሀብቱን ከመጠበቅ ጀምሮ ሀገሩን እስከ ማበልጸግ ድረስ እንዲደርስ የሚያስችለው ዋነኛ ነዳጅ አቅምና ጉልበት ቢኖር ሞራሉ (ቅስሙ) ወይም ለራሱ የሚሰጠው አዎንታዊ ግምት በመሆኑ ነው፡፡ ቅስሙ ወይም የተነሳሽነት ስሜቱ የተሰለበ የሞተ ወይም የተኮላሸ ማኅበረሰብ ማለት የተንቀሳቃሽ በድኖች ወይም ሬሳዎች ጥርቅም ማለት ነው፡፡ እንኳንና ትርጉም ያለው ቁምነገር ሊከውን ይቅርና ቢቀሰቅሱት አይሰማም ቢጎትቱትም አይነሣም፡፡ ስለዚህም ነው ሊያስከትለው የሚችለውን አደጋ ሳያጤኑ በሕዝባችን ላይ ከየአቅጣጫው የሚያዘንቡትን አግባብ ያልሆነ ነቀፋ ስድብ ዘለፋ አግባብ ያለመሆን አጽንኦት ሰጥቸ ለማሳየት የምሞክረው፡፡ በእርግጥ ሆን ብለው ይሄንን ሥራ የሚሠሩ እኩያን እንዳሉም ይታወቃል፡፡

ችግሩ የሚጀምረው ሐበሻ ወይም የእኛ ሰው እኛ ብለን አጠቃለን ጀምለን ፈርጀን ከመነሣታችን ነው፡፡ ይህ መሆኑ ሕዝቡ "እንዲህ ነን ማለት ነው?" ብሎ የተባለውን ወይም የታማውን ነኝ ለካ! ብሎ እንዲያምንና እንዲቀበል ያደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በሕዝቡ ሥነልቡናና በራስ የመተማመን ጥንካሬ ላይ ከባድ ስብራት ያስከትላል፡፡ ከዚህ የተነሣም ሕዝባችን ለገዛ ራሱ ክብር የሌለው፣ ማንነቱን በመካድ የተጠመደ፣ ሞራሉ (ቅስሙ) የወደቀ ወይም የተሰበረ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ የዚህ ድምር ውጤትም ለሥራም ሆነ ለሌላ ብሔራዊ ርብርብና ትብብር ለሚጠይቁ ዐበይት ተግባራት ተነሣሽነት የሌለው፣ ብሔራዊ ስሜቱ የሞተ፣ የራሱን ጥሎ መላ ዘመኑን ሌላውን ለመምሰል የሚጥርና ራሱን ሳያገኝ የሚያልፍ ትውልድን ማፍራት ባጠቃላይ በማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ የተዘፈቀ ማኅበረሰብ ባለቤት እንድንሆን ያደርገናል፡፡

አንድ ነገር ግን ተገንዘቡልኝ “ጨርሶ እንዲያው ምንም የሚነቀፍ ነገር የለብንም” እያልኩ እንዳልሆነ፡፡ ፍጹምነት (perfection) እንኳንና በማኅበረሰብ ደረጃ ቀርቶ በግለሰብ ደረጃም እንኳን የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጥቂት ርካሽ ሰብእና ያላቸው ሰዎች እዚህም እዚያም የፈጸሙትን ርካሽ ተግባር ወስዶ አጠቃላይ የማኅበረሰቡ ችግር አድርጎ መውሰድና ማራገብ ግን በምንም መመዘኛ ቢሆን ትክክል ሆኖ ሊገኝ አይችልም፡፡ እንደማንኛውም ማኅበረሰብ ችግሮች ሊኖሩብን ይችላል፡፡ በአንድ ነገር ላይ ግን እርግጠኛ ነኝ፡፡ እነኝህ በእኛ ማኅበረሰብ ላይ የሚጠቀሱብን የሚጠቆሙብን ችግሮችና ነቀፋዎች ሁሉ የሐበሻ ችግሮች ብቻ እንዳልሆኑና እንዲያውም ሐበሻ ከሌሎች የዓለም ማኅበረሰብ ክፍሎች አኳያ ሲለካ ሐበሻ የተሻለ ቅን፣ ቅዱስ፣ ታማኝ እንደሆነ የተለያየ ዋቢ በመጥቀስ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አንደኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕዝበ እግዚአብሔር፤ የእግዚአብሔር ልጆችና ለእግዚአብሔር ተገዥ እግዚአብሔርን አምላኪ ሕዝብ መሆኑ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሶ ይገኛል ሁሉንም መጥቀስ መጽሐፍ የመጻፍ ያህል ሊረዝም ስለሚችል ሁለት ሦስቱን በቅርብ ትውስ የሚሉትን ጥቅሶች ቦታ ብቻ ጠቅሸ ልለፍ፡- ትን. አሞጽ 9፤7 መዝ.67፤31 መዝ.71፤9 መዝ.73፤14 ኢሳ.45፤14 የሐዋ.ሥራ 8፤26 የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በሀገርና በሕዝብ ደረጃ ከአሪት ጀምሮ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኙ ሕዝቤ ልጆቼ ያላቸው ሀገሮች ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያና እስራኤል፡፡ እንደመጽሐፍ ቅዱሱ ቃል እስራኤላዊያን ሄደው ሄደው በፈተና በመውደቃቸው አሁን በሞገስ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም መሲሑን አምላካቸውን ሰቅለው በመግደላቸውና ባለመቀበላቸው፡፡ አሁን ከቀደምቶቹ ማን ብቻ ቀረ ማለት ነው? ኢትዮጵያ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የሀገራችንን ያህል ክብርና ሞገስ ያገኘ ሀገር የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ሌሎች ሀገራትን ያየን እንደሆነ እንኳንና በክብር መጠራት ይቅርና በስም እንኳን የተጠቀሱ ከእጅ ጣት የሚበልጡ አይደሉም፡፡

መእስልምና መጽሐፍትም ቢሆን ሐበሻ የተባረከ ሕዝብ ሀገሪቱም የተባረከች መሆናቸው እንደተነገረ ይሰማል፡፡ መተለይ ደግሞ ምንም እንኳን የተጋነነና ለእኛም ጭምር እንግዳ አስተሳሰብ ቢሆንም እንደነ ሆሜር፣ ሄሮዱቶስ ያሉ ጥንታዊ የአውሮፓ ሀገራት ፈላስፎችና ጸሐፍት እኛን ኢትዮጵያዊያንን “አበሳ (ኃጢአት) የሌለባቸው” በማለት በወቅቱ ያመልኩባቸው ከነበሩት አማልክቶቻቸው ጋር አቻና ባልንጀሮች እንደሆንን አድርገው ይቆጥሩን ነበር፡፡

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ይነሣል “በእርግጥ ግን ይህች በመጽሐፍ ቅዱስም ይሁን በሌሎች መጻሕፍት ብዙ የተባለላት ታላቅ ሀገር ይህች የኛዋ ኢትዮጵያ ናትን?” የሚል፡፡ ጥያቄውና ጥርጣሬው ላላቹህ ወገኖች ከብዙ ታሪካዊ መረጃዎች በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዘፍ. 2፤13 ላይ ግዮን ወይም ዐባይ የሚመነጭባትና ምድሯንም የሚከባት መሆኗን በመግለጽ መልክአ ምድራዊ አቀማመጧ የት እንደሆነ ቁጭ አድርጎታልና አዎ! በእርግጥም ያች ብዙ የተባለላት ታላቅ ኃያል የነበረች ሀገር ሌላ ማንም ሳትሆን የኛዋ ኢትዮጵያ ናት፡፡

ይሄ እንዳለ ሆኖ አሁን ላይ ሀገራችንንና ሕዝባችንን ከሌላ ጋር ለማነጻጸር በምንሞክርበት ጊዜ ማሰብ ያለብን ነገር አለ ማንን ነው ከማን ጋር የምናወዳድረው? በምን መመዘኛ ነው የምናወዳድረው? ለማወዳደር ለማነጻጸር ነባራዊ ሁኔታዎች አመቺና አግባብነትስ የላቸውም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች በቅድሚያ ሊመለሱ ይገባል፡፡ ወደ አንድ የኀሊና ቤተ ሙከራ ውስጥ ልውሰዳቹህ፡፡ እኛ ያለንበትን የድህነት ደረጃ አስቡ፡፡ ከዛም አውሮፓውያንን እኛ ባለንበት የድህነት አረንቋ ውስጥ ከተቷቸውና የሚሆኑትን ታዘቧቸው ምን እንደሆኑ ዐያቹህ? በከፋ ማኀበራዊ ቀውስ ሲናጡ እርስ በእርሳቸውም እንደ አውሬ ሲባሉ አገኛቹሀቸው አይደል? ሌሎቹም እንደዚያው ናቸው፡፡ ይሄንን ነገር ግልጽ የሚያደርግ አንድ ነገር ልግለጽ፡-

አስቦትም ይሁን በአጋጣሚ ወይም በሥራ ጉዳይ ሀገራችንን የጎበኘ ወይም በኑቁም ቢሆን በራሱ መንገድ የቃኘን ምዕራባዊ ስለኛ ምን እንደሚል አጋጥሟቹህ አያውቅም? እኛ ሐበሾች ምንም እንኳን ይህንን በመሰለ ድህነት ውስጥ ብንኖርም ከልብ የሆነ ሳቅና ፈገግታ ግን አይለየንም፡፡ ይሄንን የታዘቡ ባዕዳን እየተገረሙና እየተደነቁ “እንዴ! ሐበሾች ይስቃሉ? እንዴት በዚህ የድህነት ዓይነት ውስጥ እየኖሩ ጭራሽም ከልብ የሆነ ሳቅ ይታይባቸዋል? በሚል ግርምት አፋቸውን ሲይዙ ይስተዋላሉ፡፡ ድርጊቱ ምጸት ወይም ሽሙጥ ሊመስል ይችላል ነገር ግን አይደለም፡፡ እንዲህ ሲሆኑ ምን ማለታቸው እንደሆነ ልብ ብላችሁታል? በእናንተ ላይ ያለው ችግርና መከራ ሁሉ በእኛ ላይ ቢሆን ኖሮ ይቅርና ሳቅና ፈገግታ ልናሳይ ወደ አውሬነት ተለውጠን እርስ በእርሳችን መባላት የሚቀርልን ይመስላቹሀል? ማለታቸው ነው፡፡

እነሱን መታዘብ የሚቻለው በዚህ ብቻ አይደለም በየ ድርሰቶቻቸውና ፊልሞቻቸው (ምትርኢቶቻቸው) በእርግጥ በምንም ጉዳይ ላይ ቢሆን ሁሉንም በአንድ መፈረጅ ባይቻልም ነገር ግን ከሞላ ጎደል ሊባሉ በሚችል ደረጃ ቅናት ምቀኝነትን ከፋት ዘረኝነትን በመሳሰሉ የማንነት መገለጫዎች ምን ያህል የከፉ እንደሆኑ የማኀበራዊ ሕይዎት ጥምረትና ትስስራቸውን ደካማነት ያሳዩናል፡፡ እነዚህ የሥነ-ኪን ሥራዎች የነባራዊ ሕይዎታቸው ገጽታዎች መገለጫዎች ናቸውና፡፡ ከእኛ ውስጥ በአካል ከመሀከላቸው ተገኝተው አብረው ኖረው የሚያውቋቸውም ማንነታቸውን ያገኙት እኛ በድርሰት ሥራዎቻቸው እንደሆኑ የምንገምታቸውን ያህል ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ታሪክ አለ በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ነው በነቢዩ ኤልሳዕ ዘመን ነው ከባድ ረሀብ አጋጠማቸውና የሚላስ የሚቀመስ ከመጥፋቱ የተነሣ የእርግቦች ኩስ እንኳን ሳይቀር በዋጋው የማይቀመስ የሆነበትና ይሄንንም ኩስ ሸምቶ የመብላት ዕድል የነበራቸው ባለጸጎች ብቻ የነበሩበት ሁኔታ የተፈጠረበት ረሀብ ነው፡፡ አብዛኛው ሕዝብ ግን ነፍሱን የማቆያ አማራጭ አልነበረውም ነበር፡፡ ቢሆንም ቅሉ “በቃ! እንግዲህ ረሀቡ ይግደለን እንጅ ምን እናደርጋለን?” በማለት ለመሞት እራሳቸውን አላዘጋጁም ከእነሱ ውስጥ ባስ ያላቸው ምን አደረጉ? የገዛ ልጃቸውን እንደ በግ አወራርደው ቀቅለው በመመገብ ረሀባቸውን ለማስታገስ ሞከሩ፡፡ 2ኛ ነገ. 6፤25 ይሄንን ዘግናኝ ታሪክ የሀገሬ ሰው ሲሰማ

ሁለት ጆሮቹን ደፍኖ እሪ ሲል ብትሰሙት በፍጹም ማሳበቁ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የእኛን የረሀብ ታሪክ ተሞክሮዎችን ያየን እንደሆነ እንኳንና የገዛ ልጆቹን ሊበላ ቀርቶ ከብቶቹን እንኳን በልቶ ረሀቡን ለማስታገስ የሚጨክን ልብ የሌለው ከከብቶቹ ቀድሞ የሚረግፈው እሱ ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ ይህ ነው የእኛ የረሀብ ዘመን ተሞክሮ፡፡ ይህ ሁኔታ ያለንን የሰብአዊነትና የሞራል (ቅስም) ብቃት ደረጃ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ አንድ የሀገራችንን የጋማ ከብት፣ የአራዊት፣ የአይጡን የጉርጡን ብዛት ያየ የውጭ ዜጋ ነው አሉ "እንዴ! እነኝህ ኢትዮጵያዊያን ይሄ ሁሉ ምግብ እያለ ነው የሚራቡት?" ብሎ በግርምት ጠየቀ፡፡

ሐበሻ ግን እንዲህ ባለ የጨከነ የረሀብ ወቅት እንኳንና በባሕሉና በሃይማኖቱ የማይበሉ ብሎ እርም ያደረጋቸውን እንስሳት ይቅርና የሚበሉትን የገዛ ከብቶቹን እንኳን ለመብላት የሚጨክን አንጀት የለውም፡፡ ምክንያቱም ያ ችግር የራሱ ወይም የሰው ልጆች ችግር ብቻ ሳይሆን እየመገብኩ እገለገልባቸዋለሁ ብሎ የያዛቸውንና እነሱም የሰው ልጅ ይመግበናል እኛም እናገለግለዋለን ብለው አምነውት የተጠጉት ምግባቸውንም ከእጁ የሚጠብቁት እንደቤተሰቡ አባል አድርጎ የሚቆጥራቸው የቤት እንስሳቱም ወይም ከብቶቹም ጭምር ነውና፡፡

በእርግጥም እንደዚያ ያለ የጨከነ ረሀብ በሚመጣበት ጊዜ ያጋጠማቸውን የረሀብ ችግር ስቃይ የሚገልጹበት አፍና አንደበት አጥተው ጎሊናን በሚነካ በልኩ ሲጥመነመኑና ሲንጠራወዙ በየሜዳው ሲፈነገሉ በዐይኑ ዕያየ ቢበላቸው ምንም ያህል ቀን ፈቀቅ ላያደርገውና ከዚያ ቆርጦ ከመጣ ረሀብ ላያድነው ነገር ሊጨክንባቸው የሚችልበት አንጀት ኖሮት አያውቅም፡፡ ስለሆነው የሚሞተው ቀድሚቸው ነው፡፡ ማረጋገጥ አልቻልኩም እንጅ በዐፄ ምኒልክ ዘመን በአድዋ ጦርነት ዋዜማ ጊዜ በተከሰተው "ክፉ ቀን" በመባል በሚታወቀው የረሀብ ዘመን ወደ ሰላሌ አካባቢ ልጇን የበላች እንደነበረች የሚናገሩ አሉ ማንና የት እንደሆነች የሚጠቀስ ነገር ግን የለም፡፡ እንዲህ ብለው የሚያወሩ ሰዎችን ቀርቤ ለመረዳት በጠየኩ ጊዜም ከወሬ በዘለለ ተጨባጭ ሆነ ነገር ሊነግረኝ የቻለ ሰው አላገኘሁም ይሄንን ነገር በመጽሐፍ ሳይቀር ያስቀመጡ አሉ አሁንም ግን ተጨባጭ አይደለም፡፡ እንዲያው ዝም ብለው ሁሉንም ነገራችንን ማንነታችንን ከአይሁዶች ጋራ ማመሳሰል የተጠናወታቸው ሰዎች ከላይ ከጠቀስኩት የእስራኤሎች ታሪክ ጋር እኛን ለማመሳሰል የፈጠሩት ይመስለኛል፡፡

በ 77 ቱ ዓ.ም. የረሀብ ወቅት ነጮች እርዳታ ለማደል መጥተው የታዘቡትንና እጅግ የተደነቁበትን አንድ ነገር ልንገራቹህ፡፡ ይህ በረሀቡ ምክንያት ቀየውን ለቆ የተፈናቀለው ወገናችን የእርዳታ እህል ለመቀበል በሥርዓት ተሰልፎ ባዩ ጊዜ ያዩትን ማመን እስኪሳናቸው ድረስ እጅግ ተደነቁ "በዚህ ደረጃ የተራበ ሕዝብ እንዴት ሥርዓት ይዞ ይሰለፋል?" እያሉ በእነሱ ግምት ይሆናል ብለው የጠበቁት የገመቱት የነበረው ሰው በሰው ላይ እየተረማመደ የበረታው ደካማውን እየረገጠ በመፋጀት የቀረበውን እህል ተሻምቶ ለየራሱ መውሰድ ነበረበት፡፡ የሆነውና ያዩት ግን ፍጹም ተቃራኒውን ነው እናም እጅግ

በመደመም አፋቸውን ያዙ፡፡ ማኅበረሰባችን ይሄንን እንዲያደርግ ያደረገው እንግዲህ የደረሰበት የላቀ የሞራል (የቅስም) ደረጃው ነው፡፡

ሐበሻ ባለውና በደኅናው ቀንም ቢሆን በየምክንያቱ እየደገሰ ማብላትና ማጠጣት መገባበዝ የሚወድ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ፍቅር አክብሮትና መተሳሰብ በዚህ ይገለጻልና፡፡ ለራሱ ያለው ነገር ኢምንት ሆኖም እንኳን ከዚያችው የሚያካፍል ማኅበረሰብ እንጅ ግለኝነት የሚያጠቃው አግበስባሽ ግላዊ የሀብት ምጣኔውን ወይም የገንዘብ አቅሙን እድገት የሕይዎቱና የሕልውናው መሠረት አድርጎ የሚቆጥር የሚያስብ ማኅበረሰብ አይደለም፡፡ ይህ ዓይነት የኑሮ ዘይቤ በነጮች ዘንድ የሚታሰብ አይደለም፡፡ እነሱ የሚታመኑት እጃቸው ባለ በተጨበጠ ነገር ላይ ነውና፡፡ በእርግጥ ይህ አስተሳሰቡ ማለትም ግለኝነት በተጣባው አስተሳሰብ የግል ሀብትን የማደርጀት አስተሳሰብ ስለሌለው ምንም አልጎዳውም ማለት ሊከብድ ይችል ይሆናል ይሁን እንጅ ኅብረተሰባችን ይህ ጉዳይ ጠፍቶት ተሰውሮት ሳይሆን ከዚያ ይልቅ የማኅበራዊ ሕይዎት እሴቴን የሚያጠናክሩ መስተጋብሮች እሴቶች ይበልጡብኛል ብሎ በማመኑ እንጅ ከቁሳዊው ይልቅ መንፈሳዊው ይበልጥብኛል ብሎ በማመኑ እንጅ፡፡

እንደ ሐበሻ ይሄንን ብሎ ማመኑ የሚገርም አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከጥንት ዘመን ጀምሮ በሃይማኖታዊ መንገድ ከፈጣሪ ጋር የጠበቀ የጠለቀ ግንኙነት ካለው ማኅበረሰብ ይህ የሚጠበቅ ነውና፡፡ በጥሪት (በኢኮኖሚያዊ) አቋሙ በተወሰነ ደረጃ ቢጎዳበትም ብዙ ጥቅምም አግኝቶበታል ብየ አምናለሁ፡፡ ምን? ቢባል የምዕራባዊያን ሕይዎትን የመምራት ዘይቤ ለማኅበራዊ ሕይዎት ግምት የሚሰጥ አይደለም፡፡ የሕይዎት አኗኗር ዘይቤአቸው የተመሠረተው ግላዊና ቁሳዊ በሆነ አስተሳሰብ ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ የቱንም ያህል ሀብት ደረጃ ቢደርሱም እርካታ የሚባል ነገር ጨርሶ አይሰማቸውም በዚህም ምክንያት የሕይዎት ትርጉሙ ግራ እስኪገባቸው ድረስ ሕይዎት ተመሳሳይና አሰልቺ ትሆንባቸዋለች፡፡ ይህ ሁኔታም ብዙዎቹን ለሥነልቡና ቀውስ እያጋለጣቸው እራሳቸውን የሚያጠፉ ዜጎቻቸው ቁጥር በአንዳንድ ገዳይ በሽታዎች ከሚደርሰው የዜጎች ሞት ጉዳት ይልቅ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ለምዕራቡ ዓለም ይህ ችግር አሳሳቢ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡

ሐበሻ ግን በዚህ የመጨረሻ የድህነት ሕይዎት ውስጥ እያለም እንኳን አንጻራዊ ባልሆነና በሚገርም መልኩ ደስታ የሚሰማው ወይም ከልብ የሆነ ሳቅና ፈገግታ የማይለየው ነው፡፡ በእርግጥ ድሀ መሆንን ባይፈልግም ድህነት የሚንገበገብለትን ክብር እንደሚያስደፍር ያውቃልና ይፈራል ይጠላልም፡፡ የሐበሻ ድህነት መንስኤዎች ከምንገምተው በላይ ውጫዊና የተወሳሰበ በመሆኑ የዚህ ባዕዳን ሸር የተሞላበት ጫና የመጨረሻ ማረፊያ እያንዳንዱ ዜጋ በመሆኑ ሰለባ ሆኖ የቱንም ያህል ድሀ ቢሆንም ግን ተስፋ ቢስነት አይሰማውም ባለችው ነገር ተደስቶ ማደርን ያውቅበታል ምንም ዓይነት ፈተና

የሚደንቀው አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰብእናና ጽናት እንዲያዳብር ያስቻለውም በእግዚአብሔር ማመኑ ወይም ሃይማኖተኛ መሆኑ ነው፡፡ ሃይማኖተኛነቱ በምንም ነገር ላይ መቸም ቢሆን ተስፋ የማይቆርጥ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ተስፋ የሚያደርግ ሰው ምንም ዓይነት ፈተናና መከራ ቢያጋጥመው ያልፋል ብሎ ስለሚያስብ ተስፋ አይቆርጥም፡፡ ሐበሻ በማኅበራዊ ሕይዎቱ የሚያደርጋቸውና የሚያከብራቸው በዓላትና ክንውኖቹ በተለይም ሃይማኖታዊ የሆኑ እሴቶቹ በሥነልቡና ህክምና ወይም ጤና አጠባበቅ በኩል ከፍተኛ ጥቅም እንዲያገኝባቸውና ጽናት እንዲኖረው አስችለውታል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ በዓላትና ክንዋኔያቸው በባሕርያቸው ሥነልቡናን በማከም መንፈስን በማረጋጋትና በማርካት ተስፋን እንዲሰንቅ በማድረግ በኩል የሚስተካከላቸውና የሚተካቸው ነገር ባለመኖሩ ማኅበረሰባችንም በእነኝህ ነገሮች ተጠቃሚ በመሆኑ ነው ምንም ያህል ቢቸገር ተስፋ መቁረጥ የማይታይበት ልባዊ የሆነ ፈገግታም የማይለየው፡፡ ይህ ጽናቱ በባዕዳን ጸሐፍትና የማኅበረሰብ ጥናት አጥኚዎች (Sociologies) ሳይቀር የተመሰከረለት መለያው ነው "ኢትዮጵያዊያን በምንም ዓይነት ፈተና ውስጥ ቢያልፉ ለምንም ነገር የማይበገሩ ጽናት የባሕርያቸው የሆነ ሕዝብ ናቸው" በማለት፡፡

እንዲህ ዓይነት እሴት የሌለው ሕዝብ እንበል ለምሳሌ አውሮፓውያን እኛ የተፈተነውን ቢፈተኑ ባለፍንበት ቢያልፉስ ምን ይውጣቸው ነበር? በምን ይጽናናሉ? በምን ይረጋጋሉ? ብንል ቀደም ሲል እንደነበረው ማኅበራዊ አስተሳሰባቸው ቢሆኑ ብዙም የሚታወኩ አይመስለኝም እንደኛው ይለምዱት ይሆናል ምክንያቱም ዛሬ ላይ በዘመናዊነት ምክንያት የጣሉት ለሞራል (የቅስም) እና ለሃይማኖት ድንጋጌዎች ቦታ ይሰጡ ነበርና፡፡ አሁን ባላቸው ማኅበራዊ አስተሳሰብ ግን ጨርሶ መቋቋም የሚችሉ አይመስለኝም ምክንያቱም ሃይማኖትን ወይም ሃይማኖተኝነትን እንደ ኋላ ቀርነት ቆጥረውት ዘመናዊ አስተሳሰብ ብለው የያዙት ቁሰኝነትንና ግለኝነትን ነውና፡፡ የቁሰኝነት አስተሳሰብ ደግሞ የታመኑበት ቁሳዊ ነገር (ሀብት ንብረት) እስካለ ጊዜ ነው እንጅ በእጅ በሌለ ጊዜ ግን የማይኖር እንደ ሀብቱ ሁሉ ጥሎ የሚጠፋ በመሆኑ ለተስፋ ቢስነትና ተስፋ መቁረጥ መጋለጥ ይመጣል የዚህ ውጤት ደግሞ እጅግ አስከፊ ማኅበራዊ ቀውስ ነው፡፡

እናም ይሄንን ያልተረዱ ሰዎች መንፈሳዊና ባሕላዊ እሴቶችን ምንም ጥቅም እንደሌላቸው እንደተጎዳንባቸው አድርገው ሲናገሩ ስሰማ ይገርመኛል፡፡ ዕድሉ ያላቸውና መድረኩንም የያዙት እነሱው በመሆናቸው እነሱ በሚሰጡት ዲስኩር እንዲሁም የዘመነ ሉላዊነት (Globalization) ተጽዕኖ ሳቢያ በተለይም በከተሞቻችን አካባቢ ሞራላዊ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ የኑሮ ዘይቤአችን እየተለወጠ በተለይም አዲሱን ትውልድ በምዕራባዊያኑ ውጥንቅጥና መረን የለቀቀ የአኗኗር ዘይቤ ተጽዕኖ ስር እየጣለው መጥቷል፡፡ ይሄ ደግሞ ትውልዱን ለሞራል (ለቅስም) ድንጋጌዎች ግድ የሌለው ከግለኝነት አስተሳሰቡ የተነሣም የሀገርና የሕዝብን ጥቅሞች ከግል ጥቅሞቹ በታች አድርጎ የማየት ሕዝባዊና ሀገራዊ ኃላፊነቶችን ለመሸከም የማይችል ደካማ እያደረጉት ይገኛል፡፡

ምዕራባዊያኑ ግን ከዘመናዊው አስተሳሰባቸው ጋር እነኝህ ችግሮች የመጡባቸው ቢሆኑም ይህ አስተሳሰብ እኛ ላይ እንደሆነው ከውጭ በመጣ ጫና ገብቶ ድንገት የተከሰተ ሳይሆን አስተሳሰባቸው እየተቀየረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የራሱን ሂደት ጠብቆ እየተከሰተ የመጣችግር ከመሆኑጋር ተያይዞ ከምጣኔ ሀብታቸው ጋር እያደገ እየገዘፈ የመጣ ችግራቸው በመሆኑ ያላቸውን የደረጃ አቅም ተጠቅመው እሱን ለመቆጣጠር ችግሩን ለመቋቋም የሚያስችሉ ዘዴዎችን (ሥርዓቶችንና መዋቅሮችን) ዘርግተው ጫናው ከባድ ቢሆንም በተቻላቸው አቅም ለመቆጣጠር ሞክረዋል ወይም ሊያደርስ ይችል የነበረውን አደጋ በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ችለዋል ይህ ጥንካሬ ግን እጃቸው እስኪዝል ድረስ ብቻ ሊሆን እንደሚችል ሥጋቴ ነው፡፡

ይህ አስተሳሰብ በሉላዊነት ተጽዕኖ ሳቢያ ወደ ሀገራችን ሲገባ ግን ችግሩ ብቻ እንጅ ኢኮኖሚያዊ (ምጣኔሀብታዊ) አቅሙ አብሮ ስላልገባና እንደነሱ ችግሩን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዘዴዎችን ዘርግተን ለመቆጣጠር አቅሙ ስለሌለን የሉላዊነት አስተሳሰብ ዝግንትል በትውልዱና በሀገር ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት የከፋ እንዲሆን እያደረገው ነው፡፡ የምዕራቡን ዓለም ሥልጣኔ መውሰድ ወይም መሠልጠኑና መለወጥ ያለባቸው ነገሮች መለወጥ የሚገባ ቢሆንም ከከባድ ጥንቃቄ ጋር ቢሆን በኋላ ሊደርስብን ከሚችለው የማይጠቅም ጸጸት ያድነናል፡፡

መሠልጠን ማለት "የራስል ማንነትና ሥልጣኔ ከነአካቴው ትቶ ሌላውን መምሰል ነው" በሚል አጉል ግንዛቤ ከሆነ ግን የምንከስርበት እንጅ የምንጠቀምበት ሊሆን አይችልም፡፡ ሩቅ ሊያራምደን ወይም ሊያስሮጠን የሚችለው በእግራችል ልክ የተሠራው የራሳችን ጫማ እንጅ የሚጠበን ወይም የሚሰፋን የሌላው ጫማ ስለማይሆን፡፡ ሥልጣኔውን ተግተንና በርትተን ልንሠራበት የሚገባ ዐቢይ ጉዳያችን መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ የዛኑ ያህል ግን ለነበረንና ላለን የማኅበራዊ ሕይዎት እሴቶቻችን ጠንካራ ጥበቃና እንክብካቤ ልናደርግ ይገባል፡፡ ይሄንን ጥለው ሥልጣኔንን ብቻ ያሳደዱ ሀገራት ለምን ዓይነት ችግሮች እንደተዳረጉ በግልጽ እያየን ነውና፡፡

በተለይ ሐባሻ ያለ እነዚህ የሥነልቡና ሕክምናዎች በእንደዚህ ያለ የችግር ወቅት መኖር የሚችል አይመስለኝም፡፡ መጽሐፉስ የሚያረጋግጠው ይሄንኑ አይደለምን? "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብርስ ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን" ኤር. 13፥23 መልክ የተባለው ማንነታችንና ሰብእናችን እንጅ ጥይምናችን አይደለም፡፡ የቆዳ ቀለሙንማ ማንስ ቢሆን መቀየር ይቻለዋልን? ሲባል የተፈለገው ይህ ግልጽ እውነታ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ይቀይራል ብሎ ማሰብ ነብርም ዝንጉርጉርነቱን መለወጥ ይችላል እንደማለት ቁጠሩት የሚል የትእምርተ አንክሮ ማነጻጸሪያ ማቅረቡ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አውድ ሲታይ ማለቱ ነው፡፡

የሚገርማቹህ አሁን አሁን ግን በማያውቁትና ባልተረዱት ነገር ላይ ወይም ደግሞ ከቅጥረኝነት የተነሣ ወይም አውቀውም ሊሆን ይችላል "አዲስ ትርጉም፣ ቀላል አማርኛ" በሚል ሽፋን ማንም እያተመ እያወጣው ያለው ስመ መጽሐፍ ቅዱስ ግን "ኢትዮጵያዊ መልኩን" የሚለውን በየትኛውም ቋንቋ ቀደምት የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ላይ ያለው ቃል ቀይረው "ኢትዮጵያዊ ጥቁረቱን፣ ኢትዮጵያዊ እንደከሰል የጠቆረ ፊቱን" በሚል ቃል ቀይረው መጽሐፍ ቅዱስን ተሳዳቢና ዘረኛ አድርገውታል፡፡ አይገርሙም? እንዴት የእግዚአብሔርን ቃል ለማዛባት ይደፍራሉ የሚለውን ትተን አሁን እነዚህ ተፈጥሮን ምክንያት አድርገው እራሳቸውን የሚሰድቡ እነዚህንም ኢትዮጵያዊያን እንላቸዋለን? ልቡና ይስጣቸው እንጅ ሌላ ምን ይባላል፡፡

አሁን ቀደም ሲል ቦታ ወደ ያዝንለት የነዚያ ሰዎች አባባል ማለትም "ኢትዮጵያን አብረው መብላት እንጅ አብረው መሥራት አይችሉም፣ ለሥራ ሰነፍ ናቸው" ወደ ሚለው ልመልሳቹህ፡፡ ባዕዳን በትክክል ይሄንን ቃል ስለማለታቸው ማረጋገጥ አልቻልኩም፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸው የእኛ ሰዎች ግን ይሄ ቃል እንደ ማር ለአፋቸው እየጣፈጣቸው ሲናገሩት ትሰሟቸዋላቹህ፡፡ ይሄንን የሚል ባዕድ ካለ ግን ወይ እኛን ከቶውንም አያውቀንም ወይ ደግሞ ተንኮል አዝሏል፡፡ በሁለት ምክንያቶች፡-

1. አባባሉ አመክንዮአዊ (logical) ባለመሆኑ፡፡ የሰው ልጅ በባሕርይው አብሮ መብላትን አብሮ ከመሥራ ስለማይመርጥ፡፡ አትጋሩኝ ብቻየን ልብላው የሚያሰኝን አውሬያዊ ጠባይን ትቶ ወይም አሸንፎ ወዶና ፈቅዶ አብሮ ተካፍሎ ተስማምቶ የመብላትን ያህል ያደገና የበሰለ የሰዎች የመግባባት የመስማማት የመፋቀር የመተሳሰብ መገለጫ እሴትን የገነባ ማኅበረሰብ በማንኛውም የአመክንዮ መለኪያዎች ቢታይ አብሮ መሥራት ይቸግረዋል ወይም ይሳነዋል ተብሎ ስለማይታመን ስለማይታሰብ፡፡

2. አብሮ የመሥራትን የመተባበርንና የሥራን ጥቅም በሚገባ ተረድቶ ደቦ፣ ወበራ፣ ወንፈል የመሳሰሉትን አብሮ የመሥራት የትብብር ዘዴና ሥርዓት ፈጥሮ ለሽዎች ዓመታት ሲጠቀም የኖረንና በሥራ ባሕሉ ጥንካሬ የሥልጣኔ ቁንጮ ሆኖ አብሮ መሥራትን ባሕሉ አድርጎ እረጅም ዘመናትን የቆየን፤ አብሮ በመሥራቱ በመተባበሩና በሥራ ፍቅሩም ዛሬ ድረስ ወደፊትም ኃያላኑ ሀገራት እንኳን ሊጨብጡት ሊያሳኩት ያልቻሉትን ነጻነቱን ማስጠበቁን ጨምሮ ብርቅየ ብርቅየ እንደ ላሊበላ አብያተመቅደሳት እንደ አክሱም ሐውልት የመሰሉ የምሕንድስና የሥራ ውጤቶቹንም አሁን ድረስ ማሳየት የቻለን ሕዝብ ለእነዚህ አብሮ የመሥራትና ባሕላዊ ሥርዓቶችም አልገዛም ያለን ያፈነገጠን የለገመን ያለመጠውን ሰው የሚቀጣበት ሸንጎ፣ ምስለኔ፣ በላ ልበልሀ፣ እሰጥ አገባ ወዘተ. ባሕላዊ የፍርድ አሰጣጥ ዘዴን ዘርግቶ እየዳኘ የኖረን ሕዝብ በስም ጠርቶ አብሮ መብላት እንጅ አብሮ መሥራት አይችልም ለሥራ

ሰነፎች ናቸው ብሎ ያልሆነና ውዳቂ ተረት ሁሉ ጨምረው እየፈጠሩ ማነወር ይሄንን የተከበረ ባሕሉንና የሥራ ፍቅሩን እንዳልነበረ እንደሌለው አድርጎ በማስረሳት እራሱን እንዲንቅ እንዲጠላ ለማድረግ ወይስ ሌላ ለምን? ምንም ይሁን ምን ግን አባባሉ ምን ያህል ከፋትና ተንኮል ያዘለ ወይም አላዋቂነትና ድንቁርና የተጫነው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሄንን "ሐበሻ አብሮ መብላት እንጅ አብሮ መሥራት አይችልም" የሚለውን አባባል ከማከብራቸው ሰዎች አንደበት ሳይቀር ስለሰማሁት ነገሩን በመልካም ልተርጉመው ብየ ስሞክር ይመስለኛል ይሄንን የሚሉ ሰዎች ማለት የፈለጉት "እኛ ሐበሾች ከሌሎች አንጻር ስንታይ አሁን የሚታየው የሥራ ባሕላችን ደካማ ነው ለምን እንዲህ እንሆናለን? እንንብዝ እንጅ!" ከሚል ቁጭት የተነሣ ሕዝቡን አስቆጭቶ ለማነሣሣት ሊሆን ይችላል የሚል ምላሽ ለራሴ መለስኩ፡፡ ነገር ግን ይሄ የተባለው ያለመተባበር ወይም አብሮ ያለመሥራትና አሁን ይታያል የሚባለው የስንፍና ችግር በትክክል ያለ ከሆነ አብሮ መሥራት ባሕላችን ሆኖ እያለ ሠርተንም በማሳየት ከማንም የላቀ ጠንካራ የሥራ ባሕል ያለን ከሆነ ይሄንን ባሕሉን እንዳይሠራ አድርጎ አብሮ ተባብሮ የማይሠራና ሰነፍመስሎ እንዲታይ ያደረገው ምንድን ነው? ከመቸስ ጊዜ ጀምሮ ነው? የሚለው ነገር ሳይታይ አሁን ያለንበትን ድህነት ዕያዩ "ይህ ድህነት የመጣው አብሮ ካለመሥራት ነው ሊሆን የሚችለው" ከሚል ግልብ ግምት በመነሣት ደምድሞ ይሄንን ነገር መናገር ለመፍትሔ ፍለጋው አንዳች የሚፈይደው ነገር ይኖራል ብየ አልገምትም፡፡

እኔ የዚህን ችግር መንስኤ ለማጥናት ሞክሬ ከግላዊ ጥናቴ ካገኘሁት ምላሽ ተነሥቸ ስናገር ግን ችግሩ ከውጫዊ ተጽእኖ ጋር ተዳብሎ የተፈጠረ የፖለቲካና የአሥተዳደር ችግር የመነጨ እንጅ በሕዝባችን ላይ አብሮ ለመሥራት ያለመቻልና የስንፍና ችግር ያለብን ስለሆነ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ብዙ ጊዜ ከሰለባነታችን የተነሣ ለአንዳንድ ድክመቶቻችንና ችግሮቻችን መፍትሔ ለማፈላለግና ጥበብንም ለማሳደግ ስንሻ ወደራሳችን ከውስጣችን ወዳለው እምቅ አቅምና ሀብት ከመመልከትና ማንነታችንን ከመፈተሽ ይልቅ ለሁሉም ነገር አሻግረን ወደ ውጪ የመመልከት አባዜያች ሁልጊዜም ቢሆን እኛን ከተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ከመጣሉም በላይ ማንነታችንንም ከነ ጭራሹ ሲያስረሳንና ሲያዘነጋን ይስተዋላል፡፡ ሌላው ቀርቶ የስማችንን ያህል የምናውቀውን ሀብታችንን እንኳን እንዳናስለውልና እንዳናስታውስ ሲያደርገን ይስተዋላል፡፡

እንግዲህ ያለው እውነታ ይሄ ከሆነ ማለትም ሀገራችን ኃያል እኛም ብርቱዎች የነበርን ከሆነ ያሁሉ ሥልጣኔያችን የት ደረሰ? እሱ ይቅርና ቢያንስ ማስረጃ ሊሆኑ የሚችሉት ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ማለትም አብያተመንግሥታት፣ አብያተመቅደሳት ከነ ንዋዬ ቅድሳታቸው፣ የየዘመኑ አሻራ ያረፈባቸው ሌሎች ቅርሶች የት ደረሱ? የሚል ጥያቄ ይነሣል በእርግጥም መነሣት ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ አዎ በዓለም ውስጥ በተለያየና በተመሳሳይ ወቅት ጥንት ከነበሩት አራት ኃያላን

ሀገራት አንዷ የነበረች ሀገር፤ በወቅቱ ከነበሩት ኃያላን መንግሥታት ጋርም ጥብቅ የንግድና የባሕል ግንኙነት የነበራትና ተጽዕኖዋም የጎላ ከነበረች ሀገር ዘርፈ ብዙ የሆነ ቢቆጥሩት የማያልቅ የየወቅቱን አሥተዳደር፣ ባሕል፣ ጥበብ፣ አስተሳሰብ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ. በሚዘክሩና በሚያሳዩ ቅርሳ ቅርሶች የተሞሉ በርካታግምጃ ቤቶችና ቤተ መዘክሮች ሊኖሯት የግድ የሚጠበቅ ነው፡፡ ነገር ግን ሀገሪቱ የነበራትን ታላቅነት ሊዘክሩ ሊመሰክሩ የሚችሉ አሻራዎች በበቂ መጠን ሊገኙ አልቻሉም የት ደረሱ? የነበራትንም ሥልጣኔ ማስቀጠል አልቻለችም ለምን?

በርካታ ሰዎች ምሁራን የተባሉትን ማለቴ ነው ምሁርነቱ እንኳን ይቆያቸው ግድ የለም "ታዋቂ ሰዎች እንበላቸው እሽ እነሱ እራሳቸውን እንደ ምሁር ይቆጥራሉና ነው ምሁራን ማለቴ" ለማንኛውም እነዚህ ሰዎች በብዙኃን መገናኛዎች ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሲሞክሩ የተሳሳተ አረዳድ እንዳላቸው አስተውላለሁ፡፡ ከፊሎቹ ምን ሲሉ ሰማኋቸው? "በሀገራችን አንድም ጊዜ እንኳን ሰላማዊ የመንግሥት ሽግግር ተደርጎ አያውቅም" ሲሉ ከፊሎቹ ደግሞ "ምን የኛ መንግሥታት እኮ! አንዱ ሲነግሥ የፊተኛውን መንግሥት ሁለ ነገሩን አውድሞ አጥፍቶ ነውና የሚነግሠው በዚህ ምክንያት ስለ ቀድሞው ታሪካችን ምንም የምናውቀው ነገር የለም!" ይላሉ፡፡ ከተናገርኩት የቀነስኩትና የጨመርኩት ነገር የለም፡፡ ያንኑ የተናገሩትን ነው ያቀረብኩት፡፡ ይህ አነጋገር ምን ያህል ከሀቅ የራቀና ግብዝነት የተሞላበት አነጋገር እንደሆነ ማንም ሊረዳው የሚችለው ይመስለኛል፡፡ የሚያሳዝነው የተላለፈው በብዙኃን መገናኛ እንደመሆኑ ይሄንን የሚሰማውና ለታሪክ ዕውቀት ሩቅ የሆነው ዜጋ እነዚህ ሰዎች ያሉትን እንደ እውነት ወስዶ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ መደረጉ ነው፡፡ ምናልባትም የሀገራችንን ታሪክ የማጠልሸት የተሰወረ ዓላማ ሊኖራቸው ይችል ይሆናል፡፡

ይህ ያሉትን ነገር ማንም ዜጋ ብዙ ሳይሆን ታሪክን ለማወቅ ያህል እንኳን ጥቂት ገለጥ ገለጥ ያደረገ ሰው አባባላቸው ምን ያህል የተሳሳተ መሠረተ ቢስና እነሱንም የሚያስገምት እንደሆነ ይገነዘባል፡፡ በእርግጥ የችግሩ ዋነኛ መንስኤ ጦርነት መሆኑን አውቀውታል የተሳሳቱት ነገር የጦርነቱን መቸትና ባለቤት ነው፡፡ በእርግጥ በሀገራችን የመንግሥታት ታሪክ ሰላማዊ ያልነበሩ ሽግግሮች ቢኖሩም እነኝሁ ሰላማዊ ያልነበሩት የመንግሥት ሽግግሮች ቢሆኑም ግፋ ቢል ገልባጩ የተገልባጩን ይዘርፋል ወይም ይወርሳል እንጅ ልክ ዮዲት ጉዲትና ግራኝ አሕመድ በባዕዳን ፍላጎት ተነድተውና ለባዕዳኑ አድረው እንዳደረጉት ወይም ቱርክ፣ ደርቡሽ፣ ፋሲሽስት ጣሊያን በወረራ ጊዜ እንዳደረጉት ከባእድነትና ሀገሪቱንና ሕዝብን ለመጉዳት ካላቸው የጠላትነት ስሜት የተነሣ የጠላት ንብረት ነው በሚል የእሳት እራት ያደረገ የኢትዮጵያ መንግሥት አልነበረንም፡፡

በሀገራችን ከተደረጉት የመንግሥት ሽግግሮች በመቶኛ ቢሰላ ሰላማዊ ያልነበረው የመንግሥት ሽግግር በጣም አነስተኛ መሆኑን ከታሪካችን እንረዳለን፡፡ ይሄም ቢሆን በሌሎችም ተመሳሳይ የመንግሥት ሥርዓት በነበራቸው ሀገራትም

የነበረ የታየና የተፈጸመ ተፈጥሯዊ የሆነ ችግር እንጅ በእኛ ብቻ የተከሰተ ችግር አይደለም፡፡ ይሄ በሆነበት ሁኔታ ችግሩ በእኛ ላይ ብቻ የተከሰተ አድርጎ አለቅጥ አጋኖ ማውራቱና ባጠቃላይ ብሎ መጀመሉ ለእኩይ ዓላማ ካልሆነ እጅግ ስሕተትና ግብዝነት መሆኑን ላስገነዝባቸው እወዳለሁ፡፡

ወይም ደግሞ "ከሮም ነገሥታት ቄሳሮች አንዱ ኔሮን በ 64 ዓ.ም. የገዛ ሀገሩን ውቧን ሮምን በአንድ ምሽት ክርስቲያኖች አደረጉት! ብሎ ለመወንጀልና በእነሱ ላይ እርምጃ ለመውሰድ በማሰብ እሳት ለቆባት ወደ አመድነት ቀየራት አወደማት" የሚለውን ታሪክ ሰምተው በዚህ መቅናታቸው እንደሆነም አላውቅም፡፡ በተረፈ ግን ማንም እንደሚያውቀው በሀገራችን በነበረው ዘውዳዊ ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን የሚያዘው በዘር ወይም ከአባት ወደ ልጅ በሚደረግ የውርስ ሽግግር እንደመሆኑ መጠንና ሽግግሩንም ሆነ ዘውዳዊ ሥርዓቱን ሕዝቡ አሜን ብሎ ይቀበል የነበረበት ሁኔታ ስለሆነ የነበረው አንዳንድ "ለኔነው የሚገባው ለኔ ነው" የሚሉ ሽኩቻዎች ባይጠፉም የነበሩን የመንግሥት ሽግግሮች ከሞላ ጎደል ሰላማዊ የነበሩና የተባለውን ዓይነት ውድመት የሚያደርሱ ያልነበሩ ናቸው፡፡

ከዚህ ውጭ ዐፄ ቴዎድሮስ ሊያጠፉት ሊያከስሙት ዕድሜ ልካቸውን መከራቸውን ሲያዩበት የነበረውና አንድ መቶ ዓመታት ለሚጠጋ ዘመን የቆየው ዘመነ መሳፍንት የሀገራችን ታሪክ አካል መሆኑ ባይቀርም ከነበረን ሉዓላዊ አስተሳሰብ ወርደውና ደንቁረው ኢትዮጵያ ከሚለው ሥዕል ይልቅ ጎጥን ያቀነቅኑ ለጎጥና ጥቅማቸው ብቻ ይሠዉ ይደሙ የነበረበት ዘመን በመሆኑ ታሪካቸውና ውድመቱ ጎጥንና ጎጠኞቹን ማለትም መሳፍንቱንና የድንቁርና ሥራቸውን ብቻ የሚመለከት እንጅ የተማከለ አሥተዳደር የነበረበትን የሀገሪቱ ረጅም ታሪክ መለያና መገለጫ ሙሉ የሀገሪቱ ገጽታ አድርጎ መፈረጅና መግለጽ እጅግ አለሙብሰል መሆኑን መረዳት የሚያቅት አይመስለኝም፡፡

በነገራችን ላይ ሕዝቡ ይሄንን መንግሥታዊ ሥርዓት ማለትም ዘውዳዊውን ተቀብሎ መቆየቱ ባለመሠልጠኑ ነበር ወይም ስሕተት ሠርቷል ሊያሰኘው የሚገባ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ ይሄ የነበረ ባይሆንም ቅሉ የዚህ መንግሥታዊ ሥርዓት ምንጩ እግዚአብሔር ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ በመሆኑ፡፡ የእግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ ያልነበረ ማለቴ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው የእግዚአብሔር ሐሳብ ፈቃድ የነበረው ሀገርና ሕዝብ በሰው ንጉሥ እንዲገዙ አልነበረም፡፡ የእሱ ፈቃድና ሐሳብ የነበረው ንጉሡ እሱ ራሱ ሆኖ በነቢያቱ ምስፍና እንዲተዳደሩ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ከሙሴ ጀምሮ እስከ ሳሙኤል ድረስ አራት መቶ ዓመታት ያህል ለሚጠጋ ዘመን በሕዝቡና በእሱ መካከል ሆነው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እየተቀበሉ ከጠላቶቻቸው የሚያድናቸውና ሰልፍ የሚመሯቸውን በዚህ ውጡ በዚህ ውረዱ የሚሉ፣ የሚመክሩ የሚያስተምሩ መሳፍንትን እያስነሣላቸው ንጉሣቸው እራሱ እግዚአብሔር ሆኖ ከሙሴ ጀምሮ እስከ ሳሙኤል ያሉ መሳፍንት ሲያሥተዳድሯቸው ቆዩ፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ እንዲህ ሆነው

እንዲኖሩ ነበር፡፡ የእስራኤል ልጆች ግን የሰው ንጉሥ አሥተዳደርን በዙሪያቸው ካሉ አሕዛብ ዐይተው በእግዚአብሔር ንጉሥነት ሳይሆን እንደ አሕዛብ ሁሉ በሰው ንጉሥ መገዛት ስለፈለጉ ከመሳፍንቱ የመጨረሻ የነበረውን ነቢዩ ሳሙኤልን ንጉሥ አንግሥልን ብለው ጠየቁት፡፡ ሳሙኤል ሕዝብህ እንዲህ አለ ብሎ ለእግዚአብሐር ተናገረ፡፡ እግዚአብሔር በዚህ በእስራኤል ልጆች ሐሳብ ፍላጎትና ምኞት አዝኖ ነበር "በእነሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጅ አንተን አልናቁም" አለ፡፡ ይሁን እንጅ ነቢዩ ሳሙኤልን የጠየቁትን እንዲያደርግላቸው ሕዝቡን ስማ አንግሥላቸውም አለው 1ኛ ሳሙ. 8፤4-22፡፡ እናም በጥያቄያቸው መሠረት ሥልጣኑ በዘር የሚወረስ እንደ አሕዛብ ያለ የንጉሥ አሥተዳደር ሥርዓት ተሠርቶላቸው በዐመፃቸው ምክንያት እሱንም አጥተውት ለባርነት እስኪዳረጉና መንግሥታቸው ፈጽሞ እስኪፈርስ ድረስ በዚያ አሥተዳደር ሲገዙ ሲተዳደሩ ኖሩ፡፡ ይህ የንጉሣዊ አሥተዳደር ሥርዓት አስቀድሞ በእኛ ሀገር የነበረ ቢሆንም ንግሥተ ሳባ ቀዳማዊ ምኒልክን ከጠቢቡ ሰሎሞን ከሦስተኛው የእስራኤል ንጉሥ ወልዳ አስቀድሞ የነበረውን የንጉሣዊ መንግሥት ሥርዓት አጽንቶት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ማለትም እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ሊቆይ ቻለ፡፡ እናም ይህ በሰው ንጉሥ ሕዝብ የመገዛቱ ምርጫ የእኛ የሰዎች እንጅ የእግዚአብሔር አልነበረም፡፡ የሆኖ ሆኖ ግን ምንም እንኳ ምርጫው የሰዎች ቢሆንም እግዚአብሔር እያዘነም ቢሆን ፈቅዶታልና ነው፡፡

ሁለተኛ ይመስለናል እንጅ በዚያም ሆነ በዚህ ዞሮ ዞሮ የሚነግሠው ወይም ሥልጣን የሚይዘው አገር የሚገዛው የሚያስተዳድረው አንድ ሰው በመሆኑ፡፡ ሕዝቡ መርጦ ሾመውም ሥዩመ እግዚአብሔር ተብሎም ተቀባ ምንም ዓይነት ለውጥ ያመጣ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም አሁንም ቢሆን ሁሉም የሆነውና የሚሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ እሱ ይሁን ስላለ ብቻ የሚሆን በመሆኑ፡፡ እግዚአብሔር ሳይፈቅድ ከሱ እውቅና ውጭ ማንም ምንም ሊያደርግ ማንም የትም ሊደርስ አይችልምና፡፡

ወደ ምዕራቡ ሀገር ሄደን የዲሞክራሲ (የመስፍነ ሕዝብ) ቃፊር ናት ተብላ በምትጠራው እራሷንም እንደዛ አድርጋ በምትቆጥረው ወደ በተባበሩት መንግሥታት አሜሪካ እየተደረገ ያለውን ብናይ መሪዎቿ በሕዝብ ተመርጠው ነገሡ ቢባልም መሪዎቻቸውን ያየን እንደሆን ለዚያ ሥልጣን የመብቃት ዕድል ያላቸው የተወሰኑ ቤተሰቦች ብቻ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በተከታታይ አይሁን እንጅ ከአያት ጀምሮ እስከ የልጅ ልጅ ድረስ ነግሠው ወይም ለሀገር መሪነት በቅተው ዐይተናልና፡፡ አሁንም ወደፊትም በአሠራራቸው ምክንያት ለዚህ ሥልጣን የመብቃት ዕድሉ ያላቸው ቀደም ሲል በዚያ ሥልጣን የነበሩ ቤተሰቦች ልጆች ናቸውና የተለየ ተአምር ካልተፈጠረ በስተቀር የተለየ ይሆናል ብየ አልገምትም፡፡ እንግዲህ ሕዝብ መረጠ እየተባለም ሥልጣን ከጥቂት ቤተሰቦች እጅ እንዳልወጣ ዕያየን ነው፡፡

በርካታ ሰዎች “ሥዩመ እግዚአብሔር” ሲባል ሌላ የሚመስላቸው አሉ ሥዩመ እግዚአብሔር ማለት እግዚአብሔር የሾመው ማለት ነው ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ እንደ የእግዚአብሔር ቃል ከድሮ ጀምሮ እስከአሁኗ ሰዓት በሥልጣን ላይ የነበረና ያለ ማንኛውም መሪ ክፉንም ይሁን ደግን ቢሆን የሚሾመው እግዚአብሔር እንጅ ሌላ ማንም አይደለም፡፡ በሕዝቡ ዐመፃ የተነሣ በዚያ ሕዝብ ላይ ክፉና ጨካኝ ንጉሥ ይሾምበታል፡፡ ሕዝቡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሕጉንም የሚጠብቅ ሲሆን ደግሞ መልምና ቅን መሪ ይሾምለታል፡፡ ከዚህ ዘመን ጋራ ያለው ልዩነት የቀድሞዎቹ ይሄንን ተረድተው “እግዚአብሔር ሾመኝ ለዚህ አበቃኝ!” ብለው ለእግዚአብሔር እውቅናና ምስክርነት ሲሰጡ፡፡ የአሁኖቹ ደጎሞ በኃይል የነገሡቱ በጉልበቴ ይላሉ በምርጫ የነገሡቱ ደግሞ በሕዝብ ድምፅ ማለታቸው ነው፡፡ የአሁኖቹ ያልተረዱት ነገር ቢኖር በጉንፋን ልንወድቅ የምንችል ሆነን ሳለ ጉልበትን ወይንም በሕዝብ ልብ መወደድን ሰጥቶ ለሥልጣን የሚያበቃ እግዚአብሔር መሆኑን አለመረዳታቸውና ለዚያም እውቅና አለመስጠታቸው ነው እንጅ ከእግዚአብሔር የወጣ ከእሱ እውቅናና ፈቃድ ውጪ የሆነና የሚሆን የለም፡፡ ስለሆነም የዛሬዎቹም ሥዩመ እግዚአብሔሮች ናቸው፡፡

ብዙ ጊዜ ለንጉሣዊ ሥርዓት ጥሩ አመለካከት እንዳይኖረን የሚያደርገንና ዘውዳዊ አገዛዝንም ለውድቀት የዳረገው ነገር በነግሥታቱ ቤተሰቦችና በሕዝቡ ዘንድ ያለ የተሳሳተ አመለካከትና ግንዛቤ ነው፡፡ ይህ የተሳሳተ አመለካከት ተመሳሳይ አሥተዳደር ባላቸው ሀገሮች የባሰ ቢሆንም በእኛም ሀገር ችግሩ ነበረ፡፡ እሱ ምንድን ነው የንጉሣዊያን ቤተሰቦች እነሱም እንደማንኛውም የሰው ልጅ ሁሉ ዘራቸው ከአዳምና ከሔዋን በዚህ የማያምን ካለም ከሉሲ እንዳልሆነ ሁሉ እራሳቸውን የተለዩና ምርጥ ዘር አድርገው መቁጠራቸውና ለተቀረው ሕዝባቸው ንቀት ማሳየታቸው ሕዝቡን አስከፍቶና ለቁጭት ዳርጎ በዘር ሥልጣን የሚወረስበትን ዘውዳዊ አገዛዝ ዐፄ ኃይለሥላሴ ቀዳማዊን መቋጫው አደረጋቸው፡፡ በእርግጥ ንቀት ተፈጥሯዊ ነው የግድ ከዚህ ጋራ ብቻ መያያዝ አልነበረበትም፡፡ ሰዎች እኛ የተሻልን ነን ብለን ከማሰባችን የተነሣ ሁላችንም ቢሆን የምንንቀው አለን፡፡ በተለያየ ምክንያት አንደኛችን ሌላኛችንን እንንቃለን፡፡ ሌላው ቀርቶ በተለየ ኢጋጣሚ ከተመኛ የሆነው ገጠሬ ገጠር ያለውን የገዛ ወንድሙን ይንቀዋል፣ የተማረው ያልተማረውን ይንቃል፣ ቆንጆዋ ፉንጋዋን ትንቃለች ወዘተ.

የሰው ልጅ የቱንም ያህል ዝርያውና የቆዳ ቀለሙ ቢለያይም ዞሮ ዞሮ በሃይማኖታዊው አስተምህሮም ይሁን በሳይንሳዊው (መጣቃዊው) ምንጩ አንድ ነው፡፡ የሚታየውን ያህል የቆዳቀለምና ሌሎች አካላዊ ልዩነቶችን ያመጣው አንደኛው የአየር ንብረት ሁለተኛው የሰው ልጅ ዝርያ እየበዛ ሲመጣ አዳዲስና ልዩነቶችን የሚፈጥሩ የዘረመል ዓይነቶች መፈጠር ሦስተኛው መነሳቆል ወይም ምቾት ማጣት ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸውንም በምሳሌ ለማስረዳት ስሞክር፡-

በእርግጥም የአየር ንብረት ልዩነት የሰዎችን የቆዳቀለም ልዩነት ያመጣል፡፡ የአየር ልብረት ልዩነት በሰው ልጆች ላይ ብቻ ሳይሆን በእንስሳት በእጽዋትም ላይ ተመሳሳይ ልዩነት እንደሚያመጣ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ከእንስሳት ጥቂቶቹን ብንወስድ ፍየል ጦጣ ግመል ድብ የመሳሰሉትን ወስደን ዕንይ፡- ፍየል በየትም ይኑር በየት ያው ፍየል ሆኖ ሳለ በፀሐያማው አህጉር በአፍሪካ ውስጥ ያለ ፍየልንና በሰሜንና ደቡብ ዋልታ ውስጥ ወይም አቅራቢያ ያለውን ፍየል ብታነጻጽሩ በአየር ንብረቱ ምክንያት የተፈጠሩ መሆናቸውን በግልጽ የሚያስረዱ ብዙ ልዩነቶችን ታስተውላላቹሀ ሌሎቹም እንስሳትና አራዊት እጽዋትም እንደዛው፡፡ ከቀለማቸው ጀምሮ እስከ ጠጉራቸው ድረስ ሰፊ ልዩነቶችን ታያላቹሀ፡፡ የሰሜንና የደቡብ ዋልታ አቅራቢያዎቹ ነጫጮች ወይም አመድማዎችና ጎፈሮች (ጠጉራም) ሲሆኑ የአፍሪካዎቹ ደግሞ ጥቁር ወይም ቡኒ ጠጉራቸውም ሸላታ ናቸው፡፡ የዚህም ምክንያቱ የበረዷማ ሀገሮች እንደዚያ ዓይነት ቀለምና ጎፈራም የሆኑበት ምክንያት የአየር ንብረቱ በረዷማ ከመሆኑ የተነሣ ፍየሉ ብርዱን መቋቋም ይችል ዘንድ ጎፈራም ሊሆን ቻለ ፀሐይም ካለመኖሩ የተነሣ ገረጣ ወይም ነጣ፡፡

አንድ ሌላ ምሳሌ ልጨምር ምናልባት ብዙዎቻቹሀ የማየት ዕድል አጋጥሟቹሀ ይሆናል፡፡ ከሠላሳና አርባ ዓመታት በፊት አውሮፓውያን ባልና ሚስት ከልጆቻቸው ጋር ለጉብኝት ወደ ሀገራችን መጥተው በመጎብኘት ላይ እያሉ ባልታወቁ ሰዎች ሁለት ሕፃናት ልጆቻቸው ተጠልፈው የደረሱበት ጠፍቶ በብዙኃን መገናኛ ማስታወቂያ ቢነገርም ፈጽሞ ሳይገኙ ቀሩ፡፡ ከ 30 ዓመታት በኋላ እነኛ የፈረንጅ ልጆች ጎልማሳ ሐበሾችና ኦሮምኛ ተናጋሪ ሆነው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ምርዓየኩነት) ብቅ አሉ የሀገራቸው ኤምባሲም (የመንግሥት እንደራሴ ጽ/ቤት) ወላጆቻቸውን እንዲያፈላልግላቸው ጠየቁ፡፡ በእርግጥ ይሄንን ያህል የተጋነነ ለውጥ እንዲያመጡ ያደረጋቸው የአየር ንብረቱ ብቻ ሳይሆን ፍጹም የሆነ የእኛን የገጠር ጎስቋላ አኗኗር መኖራቸውም ነው እንደዚያ ሊለወጡ የቻሉት፡፡

እዚህ ላይ ልብ እንድትሉልኝ የፈለኩት በተለይ በወቅቱ ዜናው ሲለቀቅ የተመለከታቹሀ ሰዎች እነዚያ ከነጮች ወላጆቻቸው ተወልደው ወላጆቻቸውንም ይመስሉ የነበሩ ልጆች ከዚያ ሁሉ በኋላ በምርዓየ ኩነት ስናያቸው ግን በጣም ጥቂት ከሚባል ልዩነት በስተቀር ከእኛ የሚለያቸው ምን ነገር ነበር? እንግዲህ የአየር ንብረት በአንድ ትውልድ ላይ ይሄንን ያህል ለውጥ ማምጣት ከቻለ በትውልዶች ላይ ሲሆን ደግሞ ሊያመጣው የሚችለው ተጽዕኖ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መገመት ያቻላል፡፡ ይህ ለውጥ የእኛ ሰዎች ወደ ፈረንጅ ሀገሮች ሲሄድም ያጋጥማል ቆዳቸውን ገፈፉ እንዴ? እስኪያስብል ድረስ የሚለወጡት በአየር ንብረት ምክንያት ነው፡፡

ወደ ሁለተኛው ምክንያት ስናልፍ ማለትም የሰው ልጅ ዝርያው እየበዛና እየተራባ ሲሔድ ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት አዳዲስ የገጽታ የቁመናና መሰል ልዩነቶችን የሚፈጥሩ ዘረመልና (DNA) ንጥረ እድግ (Gene) ቅንጣቶች

መከሰቱ ዝርያው እየተራራቀ መምጣቱን ለማረጋገጥ መነሻቹህን አሁን ላይ አድርጋቹህ ወደ ኋላ በሄዳቹህ ቁጥር አሁን ካለነው የሰው ልጆች ዐይነቴ እየራቃቹህ እንደሄዳቹህ ትረዳላቹህ ያለው የመልክ ዓይነትም እያነሰ ይመጣል፡፡ ሌላው ቀርቶ እንኳንና በአፍሪካዊያንና በአውሮፓውያን ወይም በኤስያዊያን በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባሉ ሰዎች እንኳ በወንድምና በመንድም በእኅትና በእኅት መወንድምና በእኅት ያለውን በመመሳሰል ውስጥ ያለ ያለመመሳሰል ርቀት ከወላጅ በምን ያህል እንደራቁ ስናይ የሰው ልጆች በሒደት እየተለያዩና እየተራራቁ መምጣታቸውን እንረዳለን፡፡ ይህ ባይን ኖሮ ሁላችንም አዳምና ሔዋንን ወይንም ከዳባንና ሉሲን ብቻ የምንመስልና የማንለያይ እንሆን ነበር፡፡

ወደ ሦስተኛው የልዩነት መንስኤ ስንቀጥል ማለትም መጎሳቆል ወይም ምቾት ማጣት እንዴት ብሎ ነው በሰው ልጆች ላይ ቋሚ ልዩነት የሚያመጣው? የሚለውን ጥያቄ ስመልስ በአጭሩ ለማስረዳት በመጎሳቆል ወይም ምቾት እንክብካቤ በማጣት ምክንያ ሰዎች ለበሽታዎች ይዳረጋሉ ከእነኝህ የበሽታ ዓይነቶች ከፊሎቹ አንዴ ከተፈጠሩ በኋላ በዘር የሚተላለፉ ሆነው በበሽታው በተጠቁ ሰዎች ቀጣይ ትውልዶች ላይ እየተላለፉ ከእነሱ በመወለድ ብቻ የበሽታው ተጠቂ የሚኮንበት አጋጣሚ አለ ወይም በዘር ለሚተላለፉ በሽትዎች ሰለባ ይኮናል፡፡ እነኝህ በሽታዎች ደግሞ በሰዎች ገጽታና አካል ላይ ቋሚ የሆነ የልዩነት ለውጥ የማምጣት አቅም አላቸው፡፡ ከየአህጉራቱ ነዋሪዎች ከነጮች ከጥቁሮች ከቢጫዎች ከቀዮች ዝርያ ላይ በእነዚህ ዓይነት ችግሮች ምክንያት ወትሮ ከነበረው የተለየ የተለየ ገጽታና አካል ባለቤት የሆኑ ሰዎች በብዛት መኖራቸው ግድ ይሆናል፡፡ በመሆኑም እነኝህ ሦስት ዋና ዋና መንስኤዎች የሰው ልጆችን የዘር የቀለምና መሰል ልዩነቶችን ፈጠሩት እንጅ አንደኛው ከሌላኛው በሰብአዊ አፈጣጠሩ በልጦ ወይም የተለየ ምርጥ ዘር ሆኖ አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር አስቀድመን የነቀፍናቸው የንጉሣ ዊያን ቤተሰቦች እራሳቸውን የተለዩና ምርጥ ዘር አድርገው መቁጠራቸው ትክክል እንዳልነበረ እንረዳለን፡፡

ነገርን ነገር እያነሣው "ሀገሪቱ የነበራትን ታላቅነት ሊዘክሩ ሊመሰክሩ የሚችሉ አሻራዎች በበቂ መጠን ሊገኙ አልቻሉም የት ደረሱ? ሥልጣኔዋስ እንዴት ቀጣይ ሳይሆን ቀረ?" የሚለውን ጥያቄ ሳንመልስ ርቀን ሔድን አሁን ወደ ምላሹ እንሒድ የኢትዮጵያን ታሪክ በቅርበት ለሚያውቅ ሰው የዚህ ጥያቄ ምላሽ ቀላልና ግልጽ ነው፡፡ ከማንም ሀገር በላይ እጅግ ከፍተኛ በሆነ መልኩ ሀገሪቱ ከወራሪ ኃይሎች የገጠማት በርካታ አውዳሚ ጦርነቶችና ሸር ሴራቸውን መንስኤ ባደረገ በርካታ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ወደሙ ጠፉ ተዘረፉ፡፡ እጅግ ያሳዝናል ለዚህ ባለመታደላችን፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- ሀገራችን ኢትዮጵያ በረጅም ታሪኳ እጅግ በጣም በርካታ ጦርነቶችን አስተናግዳለች በአማካኝ ከዐሥር ዓመታት የዘለለ የሰላም ጊዜ ኖሯት አያውቅም፡፡ ሀገሪቱ ወደ አምስት ሽህ የሚጠጋ ዘመን ታሪክ አላት ሾስት ሽህ እየተባለ የሚጠቀሰው ሰሎሞናዊው ሥርዎ መንግሥት ከጀመረ ከቀዳማዊ ምኒልክ ወዲህ ያለው ነው እንጅ አጠቃላይ የሀገሪቱ ታሪክ አይደለምና ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ከቀዳማዊ ምኒልክ በፊት 74 ነገሥታት ሀገሪቱን አስተዳድረዋልና "የሦስት ሺህ ዓመት ታሪክ ያላት ሀገር" እየተባለ

የሚገለጸው አባባል የተሳሳተ መታረምም ያለበት ነው፡፡ በዚህ እረጅም ዘመኗ የነበሩት ቅርሶቿ ሁሉ መኖር ነበረባቸው ባይባልም ነገር ግን በርካታ የሚባል ጥንታዊና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የጥበብ፣ የባሕል የሃይማኖት የታሪክ ወዘተ. ቅርሶች ከምችት ቅርሶች በቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ነበሯት፡፡ የታሪክ መዝገቦች ቢጠፉም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቁምታ እንደምንረዳው ሀገራችን ከክርስቶስ ልደት በፊት ስትወረርም ስትወርም የነበረበት ጊዜ ስለነበረ በተወረረችባቸው ጊዜያት የየጦርነቱ ባሕርይ ነውና በርካታ ቅርሶቿ ተዘርፈው እንደተወሰዱ እንደተዘረፉ እንደተደመሰሱ እንደወደሙ መገመት ይቻላል፡፡ በታሪክ መጻሕፍት ተዘግቦ የሚገኘው ግን በ 842 ዓ.ም. እና ከዚያ ወዲህ በሀገሪቱ የተከሰተው መጥፎ የታሪክ አዳጣሚ ረዘም ላለ ጊዜ የቆየ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሀገሪቱ የነበሯትን ቅርሳ ቅርሶች እንኳን ተንቀሳቃሾቹን ሕንፃዎቹን ጨምሮ አመድ ያደረገ ሀገሪቱን ባዶ ያስቀረ ጦርነት እሳቶ ወይም ዮዲት ጉዲት በተባለች አይሁዳዊት ሴት መሪ ለ 40 ዓመታት ያህል መላ ሀገሪቱን ወራ ስታቃጥል ስታወድም ስታጠፋ የቆየችበት የታሪክ ክስተት ሀገሪቱን እጅግ ጎድቷል ቅርሶቿን ከማውደም አንጻር ብቻ ሳይሆን የነበራትን ሥልጣኔ ከማጥፋትም አንጻር ነው፡፡

ችግሩን ያንን ያህል ከባድ ያደረገውና ውጤቱንም መራራ ያደረገው የዮዲት ጉዲት ወረራ ለ 40 ዓመታት ልብ በሉ ለ 40 ዓመታት ያህል ተሸንፋ እስከተገደለችበት ጊዜ ድረስ በነበራት እጅግ ጽንፍ የያዘ አቋም ምክንያት ሀገሪቱ የነበሯትን ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶቿን እያሰሰች ማውደም ማጥፋት ዋነኛ ሥራዋ አድርጋ በመቆየቷ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ከዚያ በኋላ ለነገሡ የሀገሪቱ ነገሥታትና ሕዝቧ አዲስ ሀገርን የማቅናት ያህል ኢትዮጵያን እንደገና ማንሣት እጅግ በጣም ከባድ ፈተና ሆኖ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ሀገሪቱ የነበራትን ያህል አቅም ጉልባት ኃይል ያህልም እንኳን ባይሆን የተቻለውን ያህል ባንሠራራት ተደርጎ የኢትዮጵያን ህልውና ማስቀጠልና በሥልጣኔዋም መቀጠል እንደገና ታሪካዊ ሃይማኖታዊ ናሕላዊ ጥበባዊ ቅርሶችንም ማፍራት ተቻለ፡፡

ግን ምን ያደርጋል ከሌሎቹ አቻ ሀገሮች በባሰ መልኩ ጥንታዊ ቅርሶቿን ለትውልድ የማውረስና የማቆየት ዕድል ያልታደለች ሀገር ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ ከ 1520-1535 ዓ.ም. ድረስ በቆየው የዓረቦችንና የቱርክ ተዋጊዎችን አብሮ ያሰለፈው በግራኝ አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልቃዚ ወረራ እንደገና በአጠቃላይ ብሔራዊ ሀብቷን እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ እንዲዘረፍ ደብዛው እንዲጠፋና እንዲወድም ተደረገ፡፡ ግራኝ አሕመድ ዐፄ ገላውዴዎስን ድል አድርጎ የዚህን ያህል ውድመት ለማድረስ ካስቻሉት ምክንያቶች ሁለቱን ስንጠቅስ አንደኛው ሀገሪቱን ወሮ የቆየበት ዘመን መርዘም ማለትም 15 ዓመታት ያህል መቆየቱ ሁለተኛው የግራኝ አሕመድ ጦር የታጠቀው በወቅቱ በሀገራችን ከነአካቴው ታይተው የማይታወቁ እንደ መድፍ ያሉ ከባድና ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን የታጠቀ ብዛት ያለው የቱርክና የዓረቦችን ጦር ስላሰለፈ ነበር፡፡

ይህ ወረራ ምንም እንኳን የቆይታ ጊዜው ከዮዲት ጉዲት የወረራ ጊዜ ከግማሽ በታች ያነሰ ቢሆንም ዓላማውና አፈጻጸሙ ከዮዲት ጉዲትም ለየት ያለበት ሁኔታ ስለነበር ጉዳቱም ከብዷል፡፡ የነበሩትን የሀገሪቱን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶችና ሀብቶች በማውደምና በመዝረፍ ብቻ የተወሰነ አልነበረም ዓላማው ሀገሪቱን ጨርሶ እንዳትነሣ አድርጎ መስበር ጠፍ እንድትሆን ማድረግ ስለነበር እጅግ በጣም በሚገርም ሁኔታ ተሸንፎ እስከተባረረበት ጊዜ ድረስ የተቻለውን ያህል የሀገሪቱን የዕጽዋትና የእንስሳት ሀብቶች ጨርሶ በማጥፋት ሥራ ላይ ተጠምዶ በሀገሪቱ ያሉ ዕጽዋትን በሙሉ ለማጥፋት ደኖችን በማቃጠል ከደን ውጪ ያሉትንም በመቁረጥና ከነስሩ በማቃጠል በሀገሪቱ የቆመ ዛፍ እንዳይኖር እስከማድረግ ድረስ ዓልሞ መሥራቱ ነው፡፡ እንስሳቱንም ለ 15 ዓመታት ያህል እያረዱ ከበሉት የተረፈውን እየነዱ በመውሰድ ሀገሪቱን ባዶ አስቀርተዋት ነበር፡፡ እጅግ በርካታ ከየ አብያተ መንግሥቱና ከየ አብያተ ክርስቲያናቱ የተዘረፉት ከወርቅ ከዕንቁ በተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች ያጌጡና የተንቆጠቆጡ ቅርሳቅርሶች ሙልጭ ተደርገው ተዘርፈው ወደ ቱርክና ዓረብ ሀገራት ተወሰዱ፡፡ ባጠቃላይ ሀገሪቱን ከስር የመንቀል ሰይጣናዊ የጠላት ሥራ ነበር የተሠራው፡፡ ይህ አንገት የሚያስብር አዋራጅ ድህነታችን እግሩን ተክሎ ስር የሰደደው ያኔ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ የማይረሳው በየዋሻውና በየበረሀው ራሱን መሰወር ከቻለው ውጭ የነበረውና የተማረከው ስለም ሲባል አልሰልምም በማለቱ በሰይፍ እየተቀላ ካለቀው የተረፈው ነጻነት መለያው የሆነው ኩሩው ሕዝባችን በዓረብ ሀገሮችና በቱርክ በባርነት መሸጡ ነበር፡፡

ራሱን በየዋሻና በየበረሀው ሰውሮ የነበረው ሕዝባችንም ቢሆን የወረራው ዘመን ለ 15 ዓመታት የቆየ ስለነበረ አርሶና ቆፍሮም ራሱን ለመመገብ የሚችልበት ሁኔታላይ ስላልነበረ 15 ዓመታቱ ጊዜ እጅግ የመረረ የመከራ ዘመን ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ የሚበላው ሲያጣ በባሕሉም ሆነ በሃይማኖቱ ለምግብነት ከመዋል የተከለከሉትን እንስሳትና አራዊት ለመመገብ የተገደደበትና የተመገበበትም ጊዜ ነበር፡፡ እሱንም ቢሆን አብስለው ለመመገብ ሲሞክሩ ጠላት ጭሱን ከሩቅ ዕያየ በጭሱ እየተመራ እየመጣ እያጠፋቸው በመቸገራቸው አሁንም በባሕሉና በእምነቱ ክልክል የሆነውን ጥሬ ሥጋን የመመገብ ክልክልነት ዘፍ. 9፤4 ተላልፎ ያገኘውን በጥሬው ለመመገብ ተገደደ፡፡ ያለው ችግር በካህናቱም የተጤነ ስለነበር "ቀን ሲወጣ ንስሐ ትገባበታለህ ያገኘኸውን በጥሬው ተመገብ ከቀን ወዲህ ለሚሞተው የማይሠራ ኃጢአት እግዚአብሔር ይፍታው" የሚል ቃለ ምዕዳን በመስጠቱ ሕዝቡ አማራጭ አጥቶ የተከለከለን ነገር በማድረጉ ከመሳቀቅ አትርፎት ነበር፡፡ ነገር ግን በዚያ ክፉ ቀን በችግር ምክንያት የተለመደው ጥሬ ሥጋን የመመገብ ልማድ ተለምዶ ቀን ከወጣ በኋላም ሳይተው ቀርቶ ይሄው እስከዛሬም ድረስ ዘልቋል፡፡

ይህ ድርጊት ባዕዳኑንም "የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኦሪት ጀምሮ እግዚአብሔርን እንደሚያመልክ በመጽሐፍ ቅዱስም ጭምር የተረጋገጠ ሆኖ እያለ በኃይማኖቱ በጥብቅ የተከለከለን ነገር እንዴት ፈጻሚ ሊሆን ቻለ?" በሚል ግራ መጋባት "አይ! ሌላ ኢትዮጵያ ትኖራለች እንጅ ይሄ እንደ አውሬ ጥሬ ሥጋን ነፍሱ ሳይለይ የሚበላ ሕዝብማ ሊሆን አይችልም!" በማለት በዚህ

ምክንያት ብቻ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ሲያደርሳቸው ይታያል፡፡ ጀምስ ብሩስ "የጀምስ ብሩስ ጉዞ" በሚለው በመጽሐፉ ላይ ያስቀመጠውን ፈጠራ ጠቅሰው ፋሺስት ጣሊያኖችም ሀገራችንን በወረሩ ጊዜ ከማንም በፊት ቀድማ የሠለጠነችንና ለእነሱም የተረፈችን ከሥነጽሑፍ እስከ ዜማ ከምሕንድስና እስከ ህክምና ከሥነ-ፈለክ (የህዋ ምርምር) እስከ አሥተዳደር ሥርዓት ድረስ ስንት የተራቀቀችበትን ሀገር ፋሺስቶች "ሊግ ኦፍ ኔሽንስ" ቀርበው የተናገሩት ይሄንን የጀምስ ብሩስ ፈጠራ ነበር "ያልሠለጠኑ በሬውን በቁሙ ከነነፍሱ እያለ ከሰውነቱ እየቆረጡ በጥሬው የሚበሉ አራዊት ናቸው የማሠልጠን ግዴታ አለብን ላሠለጥናቸው ነው የገባሁት" ብሎ ነበር፡፡

ከግራኝ አሕመድ አውዳሚ ወረራ ወዲህ የመጣ ልማድ ጥሬ ሥጋ መብላት ብቻ አልነበረም፡፡ ወረራው ባደረሰው ጥፋት ሕዝቡን የሚመክሩና የሚያስተምሩ ሊቃውንትና ዐዋቂዎቂ ጠቢባኖቿ፣ መጻሕፍት በመውደማቸው በመጥፋታቸው ምክንያት ሥልጣኔዋ መውደሙና ቀጣይነት እንዳያገኝ ከመሆኑ ወይም ከመቋረጡ በተጨማሪ የሕዝቡ የመንፈሳዊነት ብቃትና ደረጃ እየወረደ በመምጣቱ ከወረራው በፊት በኅብረተሰቡ ዘንድ የማይታወቁና ያልተለመዱ ግብረ አረሚና (የአረማዊያን ሥራዎች) እና ግብረ አሕዛብ (የወራሪዎቹ ልማዶች) እየተስፋፉ መምጣት ጀመሩ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ወይም ቅምጥ ማስቀመጥ፣ ከትዳር ውጪ መማገጥ፣ ዓለማዊ ስሞችን መጠቀም ወዘተ. በሰፊው እየተለመደ መጣ ሕዝቡ ከመንፈሳዊነት እየራቀ ሔደ፡፡

እንግዲህ በእነዚህ ዐበይት አውዳሚ ጦርነቶች ነው ሀገሪቱ የነበራትን ታላቅነት ያህል ሊመሰክሩ ሊያረጋግጡ የሚችሉ አሻራዎች ሊጠፉ ሊደመሰሱ ተዘርፈው ከሀገር ሊወጡና ከእጃችን ልናጣቸው የቻልነው ሥልጣኔዋም ቀጣይነት አጥቶ ሊቋረጥ የቻለው፡፡ የቅርብ ጊዜው የእንግሊዞችና የጣሊያኖች ወረራ እንኳን ባቅሙ ስንትና ስንት ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶቻችንን አውድሟል፣ አስዘርፎም አስወስዶብናል በውጤቱም ወደ ኋላ አስቀርቶናል፡፡ ይህች ሀገር በዚህ ሁሉ የእሳት ማዕበል አልፋ በጥቂቱም ቢሆን ያንን የነበራትን ታላቅነትና ሥልጣኔ ሊመሰክሩ የሚችሉ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች መገኘታቸው ራሱ ለእኔ ተአምር ነው፡፡ እናም የሀገራችንን ቅርሶች ያወደማቸው ሥልጣኔያችንን ያጠፋው እነኚህ የባዕዳን ጦርነቶች እንጅ መንግሥት ለመውረስ የተደረጉ ጥቂት የእርስ በእርስ ጦርነቶች አይደሉም፡፡

እንደሚመስለኝ ታሪክ "አጥፍቶ እንደሚቀጣ ሕፃን" ቁጭ አድርጎ ሁላችንንም ኢትዮጵያዊያንን ካለፉ ታሪኮቻችን እንማር ዘንድ እየመከረን እየወቀሰን እያሳሰበን ያለ ይመስለኛል፡፡ ምን ያህል እንደተሰማርንና እንደተጸጸትን የየራሳችን ልቡና ያውቀዋል፡፡ እጅግ በሚያስደነግጥና በሚያሳዝን ሁኔታ ከእነዚህ ታሪኮች ኢምንት እንኳን እንዳልተማርን ጭራሽም ያንኑ ለመድገም ፍላጎቶች እንዳሉ የሚጠቁሙ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ድክመቶቻችን የምንማረው ነገር ቢኖር

ኢትዮጵያዊነትን ባለን የእምነትና የዘር ማንነት በተሳሳተ ሚዛን ለመለካት መሞከር ለባዕዳን በር እየከፈተ ይሄንን በመሰለ ማናችንንም በማይጠቅም ተወዳዳሪ በማይገኝለት ውድቀት ላይ እንደሚጥለን እንድንረዳ የሚያስገድደን ይመስለኛል፡፡

ይህ የውድቀት ታሪክ ሲያወሩት ያስከፋልና አይነሣ አይወራ ተብሎ ሊዳፈንና ሊረሳ የሚገባው ሳይሆን ጦርነቶቹ የፈጠሩትን ስሕተት አጠቃላይ አሳፋሪ ውድቀት ወይም ኪሳራ ተዘርዝሮና ተተንትኖ ሊጸጽተንና ዳግም ተመሳሳ ስሕተት ላይ ሊጥለን በማይችል ሁኔታ እንድንማርበት ሊደረግ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያዊያን ያለምንም ተጽዕኖና አስገዳጅ ሁኔታ ይሄንን ወይም ያንን የእምነት ተቋም መከተል የግልና ተፈጥሯዊ መብታቸውም ነውና ይችላሉ፡፡ ይሄንን ወይም ያንን እምነት መከተላችን ግን በዜግነታችን የግዴታ ለሀገራችን ልናበረክተው በሚገባን ቦታ ተግባርና አስተዋጽኦ ላይ በምንም ተአምር አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲያሳድርብን ልንፈቅድ አይደባም፡፡ እንዲህ እንዲሆን ከፈቀድን ግን ያለምንም ጥርጥር የጠላት መጠቀሚያ እንደሆንን መቅረታችን እንደሆን ልናውቅ ይገባል፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን የምንከተለው እምነት የፈለገውን ያህል ቢለያይና ቢራራቅ እንደ አንድ ሀገርና ሕዝብ በሀገር ጉዳይ ላይ ግን እንደተወላጅነታችን አንድ ዓይነት አስተሳሰብና ብሔራዊ መግባባት (National consensus) በቀና አስተሳሰብ ልንግባባባቸው የሚያስችሉን የጋራ የመግባቢያ ሐሳቦች (code of conduct) የግድ ሊኖሩን ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ በስተቀር የጋራ ሀገርና ትስስር ያለው ሕዝብ ሊኖረን ልንሆን አንችልም ዘለዓለማችንን ለራሳችን ሳንሆን የጠላቶቻችን መጠቀሚያ እየሆንን ስንጠፋፋ እንኖራለን፡፡ በባዕዳን ወይም በጠላቶቻችን ጣልቃ ገብነት በዚህች ሀገር ላይ የደረሰው ጥፋትና ውድመት ተጎጂ የሚያደርገው ይሄንኛውን ወይም ያንኛውን ሕዝብ ወይም ብሔረሰብ ብቻ አይደለም በእነዚህ ጦርነቶች ሳቢያ የደረሰብን ድህነት ሁሉንም ተጎጅ አደረገው እንጅ እነከሌን ብቻ ነው የሚባል አይደለም፡፡ ምናልባት ተጠቃሚ የሆኑ ካሉ ባዕዳኑ ጠላቶቻችን ብቻ ናቸው፡፡

እነዚያን ጥፋቶች በነጻና ሚዛናዊ የዜጋ ኅሊና እስከለካናቸው ጊዜ ድረስ ልንግባባና ላናወግዛቸው የምንችልበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይሄንን ቅንና ተገቢ ከአንድ ዜጋ የሚጠበቅ አስተሳሰብ አለመገንዘብ ወይም ለመገንዘብ አለመፈለግ ሌላ ተመሳሳይ ጥፋትና ውድቀት ይጋብዛል፡፡ ይህንን ቀናና ተገቢ አስተሳሰብ ለማሰብ ለመገንዘብ ባለመፈለጉ ነበር በዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመነ ምንግሥት እንደገና ከዚያ የግራኝ አሕመድ ወረራ የጥፋት ዘመን 300 ዓመታት በኋላ እራሳቸው ኢትዮጵያዊያን ሆነው እያለ ከጠላት ደርቡሽና ከግብጽ ጋር ተሰልፈው የገዛ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በተደጋጋሚ ሊወጉ የቻሉት፡፡ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛም “እነዚህ ወገኖች ኢትዮጵያዊያን ሆነው ሳለ ለዚህ ዓይነት ስሕተት የዳረጋቸው እስላም በመሆናቸው ነውና በግዳጅ ክርስቲያን ማድረግ አለብኝ” ብለው እንዲነሡና ክርስቲያን ለማድረግ እንዲያስገድዱ ያደረጋቸውም በተሳሳተ ግንዛቤ የተሳሳተ አቋም ይዘው የገዛ ሀገርና ሕዝባቸውን የሚያጠቁ ወገኖች ድርጊት ነው፡፡

ይንን ስር የሰደደ የተሳሳተ ግንዛቤ ችግር ለመቅረፍ ምንም የሠራነው ሥራ የለምና አሁንም በዚህ ዘመኑ ትውልድም ይሄ ችግር ጎልቶ ዕየታየ ነው፡፡ እኔ ልጅ ሆኘ ያየሁት ነው የእስልምና ተከታይ የሆነ የጎረቤት ልጅ ደርግ ለብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ሊያዘምተው ይይዙታል እኔን አይመለከትም ለማለት ፈልጎ ምን ብሎ እንደመለሰ ታውቃላቹህ? "እኔ እኮ እስላም ነኝ" እስላም ቢሆንም ኢትዮጵያዊ መሆኑንና በዜግነቱም ያለበትን ግዴታ ጨርሶ አያውቅም ነበር እንደሱ ግንዛቤ እስላም የሆነ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ላይ ኃላፊነት የለበትም፡፡ አንዴ ደግሞ ወንድሜ ምን አጋጠመው በወቅቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን ከአቻው የግብጽ ቡድን ጋር የሚያደርገውን ግጥሚያ በስሜት ተውጠው በጉጉት እየተመለከቱ እያሉ የግብጽ ቡድን ጎል ያገባል ጎሉ እንደገባ የእስልምና ተከታይ የሆነ ጓደኛቸው በስሜት ዘሎ መነሣቱንና መጮሁን ሳያውቀው ደስታውን ሲገልጽ ሁሉም ታዘቡት ዐይንህ ላፈር አሉት፡፡ በኋላም ውግዘቱና መገለሉ ሲበዛበት ምን አላቸው "አይ እኔ እኮ የእኛ ቡድን ያገባ መስሎኝ ነው" በማለት ለማስተባበል ሞከረ፡፡

ብዙዎቻችን እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ገጠመኞች ሊያጋጥመን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ በወገኖቻችን ላይ ያለው ብዥታ እዚህ ድረስ ነው ይህ ነገር ቀላል መስሎ ይሰማቹህ ይሆናል፡፡ ነገሮች ሁሉ የሚጀምሩት ከእንደዚህ ዓይነት ግንዛቤዎች ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸው ወገኖቻችን በርካቶች ናቸው፡፡ ችግራቸው ሀገርንና ማንነትን ከሚከተሉት እምነት ለይተው ለማየት አለመቻል ነው፡፡ ይህ ችግር ያልተማሩ ዜጎቻችን ችግር ብቻ አይደለም እንዲያውም በተማሩት ይብሳል፡፡ የሚገርም ነው! የተማሩ ሆነው ሳለ ሀገርና ማንነት ከእምነት ጋር ያለውን ልዩነት ጠንቅቀው ለመረዳት ሳይችሉ ቀርተው የባዕዳን መጠቀሚያ በመሆን ከሀገራቸው ጥቅሞች በተጻራሪ መቆማቸው፡፡ ስለሆነም ሀገራችንን ከሌላ ዙር ተመሳሳይ ችግር መታደግ ካለብን በእንዲህ ዓይነት የተሳሳተ የአስተሳሰብ ችግር ውስጥ ያሉ ወገኖቻችንን ከተሳሳተ ግንዛቤያቸው ወጥተው የባዕዳን መጠቀሚያ በመሆን እራሳቸውንና ሀገራቸውን እንዳይጎዱ ሀገርንና ማንነትን ከእምነት ለይተው እንዲያዩና በዜግነታቸው በኢትዮጵያዊነታቸው ያለባቸውን ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን የመጠበቅ ግዴታ እንዲያውቁና እንዲረዱ ከትምህርት ሥርዓቱ ጀምሮ አንዳች ዓይነት ሀገራዊ መግባባት እንዲኖር የማድረግ ሥራ ዛሬ ነገ ሳይባል ጊዜ ሳይሰጠው ሊሠራ ይገባል፡፡

ይሄ ችግር ያለው በእስልምና ተከታይ ወገኖቻችን ብቻ አይደለም በቅኝ ግዛት ሰላዮች በአውሮፓ ሚሲዮኖች መሠረቱ ተጥሎ ዛሬ ላይ በርካታ ለመሆን የበቁት የፕሮቴስናንት የካቶሊክና መሰሎቻቸው ተከታዮችም ተመሳሳይ ችግሮች አሉባቸው፡፡ ለነገሩ ሰባኪዎቻቸውም እነሱን እየሰበኩ ከነበራቸው ሃይማኖት ሲያስኰዷቸው ለምን ዓላማና በምን መልኩ መቅረጽ እንዳለባቸው ያውቁ ስለነበርና በዚያም መልክ ስለቀረጹዋቸው ለሀገራቸውና ለማንነታቸው ይቆጫሉ ይቆረቆራሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ 1990 ዓ.ም. ላይ ሸአቢያ ጦርነት በከፈተ ጊዜ ይሄንን ጥቃት ለመመከትና ለመቀልበስ ሀገር ከዜጎቿ ርብርብ በምትጠይቅበት ወቅት በፕሮቴስታንት ዘርፍ ያሉ ወገኖቻችን "የመንፈስ

መልዕክት" እያሉ በየአዳራሹ ያሰሙት የነበረ መልእክት ይሄንን ያሳየናል "እኛ ሀገራችን በሰማይ ነው በምድር ሀገር የለንም ይሄ ያንተ ሀገር ይሄ የኔ ሀገር ይሄ ያንተ ድንበር ይሄ የኔ ድንበር ነው ማለትና ጦር ማሰለፍ የተጠላና ከክፉ መንፈስ ነው" ወዘተ. እያሉ ዛሬ ድንገት ተነሥተው የሆነ ሀገር ቢሔዱና መኖር ቢፈልጉ እንደሚሉት ሁሉ "አንተ ማን ነህ ከየት መጣህ" ሳይላቸው እንደፈለጉ የመኖር የመውጣት መግባት መብት ያላቸው ይመስል እንደዚያ እያሉ ተከታዮቻቸውን በመስበካቸው የወያኔ አገዛዝ በእነሱ ላይ እርምጃ ለመውሰድ የተገደደበት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው፡፡ ከዚህ ውጭ ባላቸው አጠቃላይ ማንነት ስናያቸውም ለሀገራችን እሴቶች ባሕል ታሪክ ማንነት ጠላቶችና እነሱን በማጥፋት ላይ እራሳቸውን የጠመዱ ናቸው፡፡ ከቆዳቸው በስተቀር ኢትዮጵያዊነት አይታይባቸውም እንዲታይባቸውም አይፈልጉም፡፡

እነዚህ እነዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ባዕዳን የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሠሩት ሥራ እያደር በኢትዮጵያዊነት ላይ ምን ያህል አደጋ እንደጋረጠና ወደፊትም ከነአካቴው የማጥፋት አቅም ሊኖረው እንደሚችል ያሳየናል፡፡ እጅግ በጣም የሚገርመኝ ነገር እነዚህ ጠላቶቻችን ወገኖቻችን እንደ ሮቦት ማሽን (መሳሌ ፍጥረት ማሳልጥ) የፈለጉትን ነገር ሞልተውባቸው ጭነውባቸው ከማንነታቸው ከገዛ ሀገራቸው ጥቅም በተጻራሪ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ መቻላቸው ነው፡፡ እንግዲህ ያለው ነገር የሚያሳየን ነገር ቢኖር ኢትዮጵያዊነትን ለመታደግም ምን ያህል ሥራ እንደሚጠብቀን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም ይሄንን ብዥታ ከዜንች ጎሊና ላይ የማጥራቱ ነገር የሚያከራክርና ቸል የሚባል ጉዳይ ሊሆን አይገባም፡፡

እናም መንስኤዎቹ ከላይ የተጠቀሱት ናቸው፡፡ ነገር ግን ጠላቶቻችን ሀገራችንን ሲወጉ ሲያዳክሙና ሲያደኽዩ የኖሩት በአፈሙዝ ወይም በሰይፍ ብቻ አልነበረም፡፡ ከፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ሸሮችና ሴራዎች በተጨማሪ ማኅበራዊ ቀውሶችን፣ የምጣኔ ሀብት ድቀቶችንና የሥልጣኔ ውድቀትን ሊያስከትል የሚችም ሴራ ያሴሩ ነበር ለሴራዎቻቸውም አጥጋቢ ውጤት ማግኘት ችለዋል፡፡ ለምሳሌ ፖርቹጋሎች ወደ ሀገራችን በገቡበት በ 16 ኛው መቶ ክ/ዘ በወቅቱ የነበረን የኀጅ ኢንዱስትሪ (ምግንባብ) መሠረት ያለውና ተስፋ ሰጪ አቅጣጫን እየተከተለ ያለ እነሱ ወደደረሱበት ቦታ የሚወስድ መንገድ ላይ መሆኑን በመረዳታቸውና ማጨናገፍ ስለፈለጉ ሞያተኛውን ከሕዝቡ ነጥሎ የሚያስመታ ሴራ ሸረቡ፡፡ ሸረቡና "እኛ በሀገራችን ብረት ቀጥቃጮች፣ ሸክላ ሠሪዎች፣ አንጠረኞች ወዘተረፈ. ቡዳዎች (ክፉ መንፈስ ያለባቸው) ናቸው፡፡ ሰውን እየበሉ ያስለፈልፋሉ ልቡን አድክመው አእምሮውን ነስተው አሳብደው ይገላሉ፡፡ እነሱን ሰብስበን ካጠፋን በኋላ ነው ሰላም ያገኘነው፡፡ እናንተም እንዲህ ብታደርጉ እነሱ ስለበሏቸው የታመሙ ሕመምተኞቻቹህን በየጸበሉ ይዞ ከመንከራተትና ወገኖቻቹህን ያለቀናቸው ከማጣት ትድናላቹህ ነጻ ትሆናላቹህ!" እያሉ ከቤተመንግሥት እስከ ታች ኅብረተሰቡ ድረስ ወርደው በመስበክ በመመረዛቸው የዋሁ ቅኑ ሕዝባችን እውነት መስሎት በሞያተኛ ወገኖቹ ላይ በወሰደው የተለያየ ዓይነት እርምጃዎች፡፡ ከሥልጣኔው እስከ ምጣኔ ሀብቱ ድረስ ውድቀትና ኪሳራ ሊደርስበት ማኅበራዊ ቀውስ

ውስጥም ተዘፍቆ እንዲቀር አድርጎታል፡፡ ከዚያ ዘመን ጀምሮ ይሄንን ሰይጣናዊ ሴራ የነቁበትና ከሚያደርሰው ጥፋት ሀገርንና ሕዝብን ለመታደግ የሞከሩ የጣሩ ቢኖሩም “አንድ ሞኝ የተከለውን ዐሥር ሊቃውንት አይነቅሉትም” ይባላልና ሸረኞችም ከስር ከስር ሥራቸውን ይሠሩ ስለነበር ሸረኛ አስተሳሰቡ እንኳን በዚያ ዘመን ዛሬም ሊጠፋ አልቻለም፡፡

አንዳንድ ግለሰቦች ““ፖርቹጋሎች “ሰብስበን አጠፋናቸው” ማለታቸው ስሕተት ይሁን እንጅ ሞያተኞችን የቡዳ መንፈስ ያለባቸው አድርጎ የሚቆጥረው አስተሳሰብ ግን በግሪኮችና በላቲኖች ዘንድም በዚያ ዘመን የነበረ በመሆኑ ለሴራ ብለው ያደረጉት አይደለም”” ብለው የሚከራከሩ አሉ፡፡ የሆነ ሆኖ ግን አስተሳሰቡን በሀገራችን ምን ውጤት እንዲፈጥር እንደተጠቀሙበትና ፍላጎታቸውን እንዳሟሉበት ስናይ የከፋት መሆኑን ለመረዳት የሚያዳግት አይመስለኝም፡፡ እናም ሀገራችን ከጠላትና ከወራሪዎች ይሰነዘርባት ከነበረው ሁለንተናዊ ጦርነት ይሄንና ይሄን የመሰሉ የሴራ ውጊያዎችም ለውድቀታችን ሌላ መንስኤ ናቸው ለማለት ነው፡፡

እስኪ ደሞ ወደ ሌላው የሐበሻ ልጆች ሐበሻን ወደ ሚያሙበት የሐሜት አባባል እንለፍ ይሄን ሐሜት መጀመሪያ ያነሡት ከ 30 እና 40 ዓመታት በፊት “ታላላቅ” የሚባሉ ደራሲያኖቻችን ናቸው “ሐበሻ ሆዳም ነው ያለ ሆዱ ምንም አያውቅም” ይላሉ “ያለ ሆዱ ምንም አያውቅም” ለሚለው የሥልጣኔ ፍሬዎቹን በማየት በቀላሉ ሊዳኝ የሚችል ጉዳይ በመሆኑ አባባሉል ለአንባቢ ትዝብት ትቸ “ሆዳም ነው” ወደሚለው ልለፍ፡፡ ይሄም ቢሆን የሚያከራክር ሆኖ ሳይሆን መገለጽ ያለባቸው ቁምነገሮች ስላሉ ነው የምናየው፡፡ ይገርማል! ሐበሻ ሆዳም ነው! መባሉ፡፡ አይገርማቹህም? ስለ ምግብ ስናነሣ ሐበሻ የሚመገባቸውን የምግብ ዓይነቶች ማየት ይኖርብናል፡፡ በጥቅል ሐበሻ ሲባል በውስጡ በርካታ ብሔረሰቦች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በምግብ ዙሪያ ሁሉንም የሚያመሳስላቸው ነገር አለ በሃይማኖታዊና በባሕላዊ አስተሳሰብ የተነሣ ለምግብነት ከምንጠቀምባቸው ፍጥረታት የማንጠቀምባቸው የምንጠየፋቸው እጅግ ይበዛሉ፡፡ ለምግብነት የምንጠቀምባቸው በጣት የሚቆጠሩትን ብቻ ነው፡፡ የሌሎቹን የዓለም ክፍሎች ማኅበረሰቦች ያየን እንደሆነ ግን “በአየር ከሚበሩት ከአውሮፕላን በምድር ከሚሽከረከሩት ተሽከርካሪዎች በስተቀር ነፍስ ያለው ፍጥረት በሙሉ ጥርግ አድርገው ነው የሚበሉት” እስኪባሉ ድረስ የሚመርጡት ነገር የለም፡፡ አሁን ታዲያ ሐበሻን ሆዳም የሚያሰኘው ምኑ ነው? ጥዩፍ ሆኖ መርጦ ጥቂቶችን ለምግብነት መጠቀሙ በርካቶቹን ተጠይፎ መተው ነው? ሆዱን የሚያሰኘው ወይስ የሚመገባቸውን ዓይነቶች በብዛት እያግበሰበሰ የሚበላ ሆኖ?

የሐበሻን የመመገብ መጠን ያየን እንደሆነ ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸር የሰማይና የመሬት ያህል ርቀት አለው፡፡ ሌሎቹ ይበላሉ የሚለው ቃል አይገልጻቸውም ምናልባት ይጠርጋሉ ይከታሉ የሚለው ቃል ከገለጻቸው እንጃ፡፡ እንደ ጅብ ነው የሚከቱት በምግብ ሰዓት ሲበሉና የሚበሉትን የምግብ መጠን ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የምናየው እኔንም እንዳይጨምሩኝ

በሚል ፍርሐት ደንገጥ ማለታችን አይቀርም፡፡ ይሄ የሚበሉትን የሚከቱትን ሁሉ በእርግጥ ሆዳቸው ውስጥ ነው ወይስ ሌላ ነገር አላቸው? ብለን ግራ መጋባታችን ሁሉ የማይቀር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ሰውነታቸው የገዘዘፈውና ከልክ በላይ ለሚባል ውፍረት የሚዳረጉት፡፡

ወደኛው ስንመጣ ግን ኖረንም አልኖረን በጾሙም በምኑም ምክንያት የምንመገባት የተመጠነች ናት፡፡ የምግብ ዓይነቴዎቻችን ለምግብነት ከምንመርጣቸው እንስሳት አእዋፍ ዓሣት ውስንነት የተነሣ ከሌሎቹ አንጻር ሲታይ በጣም ውስን ናቸው፡፡ ለምግብነት ከመረጥናቸው ውስንነት የተነሣም ብቻ ሳይሆን በሐበሻ ፍልስፍና በመጠን መመገብ የሃይማኖቱ መሠረታዊ ፍልስፍና ስለሆነ የምግብን ነገር እንደነገሩ አድርጎ እንጅ ሙሉ ትኩረት ሰጥቶ ሥጋየን እንዴት አድርጌ ላድልበው ብሎ ሥጋን ስለማድለብ በምግብ ሥጋን ስለመንከባከብ ጊዜ ሰጥቶ አስቦ አውጥቶ አውርዶ የተፈላሰፈበት ወቅት ኖሮ አያውቅም፡፡

ታዲያ እንግዲህ ጸሐፊያን ደራስያን ሐያስያን ተብየዎቹ ከየት አምጥተው ነው የሌለበትን አምጥተው በድፍረት ሳይከብዳቸው "ሆዳም" ነው ሊሉት የቻሉት? የሚገርመው ሐበሻ የጃንሆይን ግብር ለመብላት ያደርገው የነበረውን ግብግብ ለሆዳምነቱ ማስረጃ አድርገው ሁሉ ያቀረቡ ደራስያን ጸሐፊያን መኖራቸው ነው፡፡ ዕታቸው እጅግ ግልብ ነው፡፡ ሐበሻ የነገሥታቱን ግብር ለመብላት በግብሩ ሥፍራ ያንን ያህል ይጋደል የነበረው ሆዳም ስለሆነ ወይም የሚበላው ስላጣ ወይም ለሆዱ ስብድብድ ስለሆነ ሳይሆን ነገሥታቱ "በእግዚአብሔር የተቀቡ" መሆናቸው ስለሚታመንና ያ ግብርም በጳጳሱ በኋላም በፓትርያርኩ ስለሚባረክ የእግዚአብሔር በረከት አለው ተብሎ ስለሚታመን ያን በረከት ለማግኘት እንጅ ሆዳም ስለሆነ ወይም የሚበላው ስለሌለው አልነበረም ከመኳንንቱ እስከ ጭፍራውና ተራው ሕዝብ ድረስ የንጉሥን ግብር ለመብላት ይጋደል የነበረው፡፡ ሕዝቡ በጳጳሱ በተባረከው በእግዚአብሔር በተቀባው ንጉሥ ግብር ካለው መተማመን የተነሣ እንዲያውም ምን እስከማድረግ ይደርሳል መሰላቹህ ልጆቹ ጳጳሱን አግኝተው የመባረክ ዕድል ባያገኙ ከዚያ የንጉሥ ግብር ፍርፋሪም ቢሆን ወስዶ ቢያቀምሳቸው "ይባረካሉ ከዚያ በኋላ ወንጆች ልጆቹ ዶሮን በግን የመሳሰሉትን ለምግብነት የሚውሉ የቤት እንስሳትን መባረክ (ማረድ) ይችላሉ" ብሎ እስከማመን ይደርሳ፡፡ በእርግጥ የእምነት ጉዳይ በመሆኑ የቤተክርስቲያኗ አስተምህሮም ይህ አስተሳሰብ ትክክል አይደለም አይልም፡፡ እናም የሐበሻ በየንጉሡ ግብር የሚጋፋ የሚጋደልበት ምክንያት ይሄ እንጅ ያውም በዚያ ኑሮ እጅግ ርካሽ በነበረበት ዘመን በግ ቆዳ ምላሽ በነጻ ይበላ በነበረበት፣ ዶሮ በስሙኒ በዐሥር ሳንቲም በዓት እንቁላል ይገዛ በነበረበት ዘመን የሚበላው አጥቶና ሆዳም ወይም ለሆዱ ስብድብድ ስለሆነ አይደለም እንዲያ ያደርግ የነበረው፡፡

ጨምረው የሚተቹበት ነገርም አላቸው "ሐበሻ ያለ ሥጋ ምግብ ያለ አይመስለውም ለሐበሻ ከምግብ ዓይነቱ ሁሉ ምግብ ማለት ሥጋ ነው" የሚል፡፡ ነገር ግን ለሐበሻ ብቻ ሳይሆን ለማንስ ቢሆን ውዱ የምግብ ዓይነት ከሥጋ ውጭ ሌላ ምን አለ? አውሮፓና አሜሪካስ ቢሔዱ አንድ ኪሎ ሥጋና አንድ ኪሎ ድንች ወይም ጥቅል ጎመን ወይም አተር ወይም ቲማቲም ወዘተ. ዋጋቸው እኩል ነው እንዴ? በጣም እኮ የሚገርምና እንጭጭ ትችት ነው፡፡ በቀላሉ እንዲህ ብለው ቢያስሉት ሊደርሱበት የሚችሉበትን እውነት ለራሳቸው ግራ ተጋብተው ሌላውንም ግራ ለማጋባት ይሞክራሉ፡፡ ይሄ አስተሳሰባቸው ለራሳቸው ያላቸውን አግባብ ያልሆነ ዝቅተኛ ስሜትና በባዕዳኑ ተወርውረው ያሉበትን የማንነት ቀውስ ያሳይ እንደሆነ ነው እንጅ ቢዘቀዘቅ ጠብ የሚል እውነት ያለው አስተሳሰብ አይደለም፡፡ ምድረ ቅጥረኛ፡፡

አንዳንዶች ሐበሻን ሆዳም ነው ሲሉ በዚህ ዘመን ያሉትን ጥቂት ሰዎች ባሕርይ የአጠቃላይ የሕዝቡ እንደሆነ አድርገው በማሰብ "ነጻነቱን ለሆዱ ሲል አሳልፎ ይሰጣል!" የሚለውን አገላለጽ ይጠቀማሉ፡፡ ፍጹም ማስተዋል የጎደለውና የሐበሻን ማንነት ጨርሶ የማይገልጽ ደካማ አባባል ነው፡፡ ሐበሻ ለነጻነቱ ቀናኢና ከሱ የሚያደርሰው ነገር የሌለው ከባባድ የመሥዋዕትነት ዋጋ ከፍሎ ነጻነቱን አስጠብቆ የኖረ እንደሆነ ማስተዋል አልቻሉም፡፡ በአሁኑ ሰዓት በወያኔ አገዛዝ ያለውን ሁኔታ በማየት ባልገባቸው ነገር ላይ ይሄንን የተሳሳተ ሐሜት ይገልጻሉ፡፡ ሕዝቡ በወያኔ እየደረሰበት ያለውን የማይቻል ነገር እየቻለ ምንም እንዳልተፈጠረ በዝምታ መመልከቱ ሆዳም ስለሆነና ነጻነቱን በሆዱ ለውጦ ሳይሆን ሀገሩን ከባሰ ጥፋት ለመታደግ ለማዳን ለጊዜው ያለው ብቸኛ አማራጭ ጥንቃቄ የተሞላበት ሰፊ ትዕግስትና ደንዳና አንጀት ስለሆነ እንጅ ለሆዱ ሲል ነጻነቱን በሆዱ ቀይሮ አይደለም፡፡ ወያኔ ከገባ ጀምሮ ታሪክን ማንነትን ብሔራዊ ጥቅምን ሉዓላዊነትን መጫወቻ መቀለጃ ሲያደርግ ሕዝቡ ዝም ማለቱ አንዳች ነገር ቢያደርግ ወያኔ ኃላፊነት የሚሰማው አካል ባለመሆኑ በቂም በቀል አስከትሎ የሚወስደው እርምጃ ሀገሪቱን እስከማፈራረስ ሕዝቡንም እርስ በእርስ እስከማባላት የሚደርስ ስለሆነና ከዚህም የሚያተርፈው ምንም ነገር እንደሌለ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ የማያረጅ አርጅቶም የማይጠፋ የማይከስም ምንም ነገር የለምና የፈራው አደጋ ሳይደርስ ለመቅደምና ወያኔን ለመገላገል የሚያስችል ምቹ አጋጣሚ እስካላገኘ ጊዜ ድረስ ወያኔን ከነግፍ አገዛዙ ከነለሀጩ ከነ ብልግናው ከነእርኩሰቱ መሸከም ይሻላል በማለት ዳኝነቱን ለጊዜና ለእግዚአብሔር በመስጠቱ ነው፡፡ ባለ አእምሮ ለሆነ ሁሉ ይህ ሁኔታ በግልጽ የሚታይ ነውና በቀላሉ ይረዳዋል፡፡

ሌላው እነዚህ በመሀላችን ተሰግስገው የባዕዳን ቅጥረኛ በመሆን ቅስማችንን ለመስበር የሚጥሩ ወገኖች ሲያደርጉ የሚታዩት ነገር ምንድን ነው ሥነ ቃሎቻችንን አባባሎቻችንን ተረቶቻችንን እየጠቀሱ አስተሳሰባችን የተሳሳተና ደካማ እንደሆነ እንድንረዳ እንድናምን ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት ነው "ሐበሻ ለልጅ ክብር የለውም ክብር አይሰጥም፣ ለልጆች ቦታ ሰጥቶ በውይይት አያሳትፍም" ይሉና አባባሎቹ የሚያረጋግጡትም ይሄንን ነው በማለት የሚከተሉትን አባባሎች ይጠቅሳሉ "ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም፣ በጫጩት ፊት ፈንግል አይወራም፣ የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ

ጥሬ፣ ልጅ ይሮጣል እንጅ አባቱን አይቀድምም" የመሳሰሉትን ከልጅ ጋር የተያያዙ ተረቶቻችንን በመጥቀስ እኛ ሐበሾች ለልጆች ክብርና አክብሮ እንደሌለን አድርገው ለማሳየት ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡ ሰዎቹ ማስተዋል ስለማይችሉ መረዳት አይችሉም እንጅ በእነኚህና በሌሎቹም ተረቶቻችን ወይም አባባሎቻችን ላይ ምንም ስሕተት የለም ተረቶቹ አባባሎቹ እውነታው ምንም ይሁን ምንም ከእውነታ ላይ በመመሥረት የሚወጡ ናቸውና፡፡ የተረትና ምሳሌዎች ዓላማም ይሄው ነው ክስተቶችን ገጠመኞችን ኩነቶችን በተቀመረ በተመጠነ አገላለጽ እንዳሉ ማስቀመጥ፡፡ አንድ ነገር ተረት ሥነቃል ወይም አባባል የሚወጣለት የሚወደድ ነገር ከሆነ ብቻ አይደለም ሰዎቹ ያላወቁትና መረዳት ያልቻሉት ይሄንን ነው፡፡

ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሱትን ብናይ "ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም" ማለት የልጅ አቅም ጉልበት እንደ አዋቂ ብርቱ አይደለምና ሊያቦካ የሚችለው ያቅሙን ታክል የተመጠነች ናት፡፡ በአቅሙ ያቦካት ደግሞ አነስተኛ ትሆናለችና ከቁርስና ከምሳ አልፋ እስከ እራት የማትበቃ ትሆናለች ማለት ነው፡፡ በተረቱ ለመግለጽ የተሞከረው ልጆች እንደ ልጅነታቸው አቅማቸው የተወሰነ ነው ብዙ ሊጠበቅባቸው አይገባም የሚለው ሐሳብ ነው፡፡ ይሄ ታዲያ ምኑ ነው ስሕተቱ? እንዲያውም ሕፃናት ከአቅማቸው በላይ እንዲሠሩ እንዳይገደዱና እንዳይበዘበዙ መብታቸው እንዲጠበቅ ይመክራል እንጅ የሚያመጣው ችግር ምንድን ነው? "ልጅ ይሮጣል እንጅ አባቱን አይቀድምም" የሚለውም በተመሳሳይ የሚታይ ነው ልጅ እንደመሆኑ መጠን ከልምድና ከዕድሜ የሚገኙት ዕውቀቶችን እንዳለመያዙ ዕውቀቱ የተሟላ አይደለም ውስንነት አለበት ማለት ነው ይሄም እውነት ነው፡፡ "በጫጩት ፊት ፈንግል አይወራም" የሚባለውም እንዲሁ እውነት ነው ይህ ጥቅስ የሚጠቀሰው በልጆች ፊት ምሥጢር ማውራት ተገቢ እንዳልሆነና ለችግር እንደሚጋርግ ማስገንዘብ ሲፈለግ ነው "ልጆች ምሥጢር አያውቁም ምሥጢር ነው ብላቹህ ብትነግሯቸውም አይደብቁላቹህም በዚህ መሀል ለችግር ልትዳረጉ ትችላላቹህ" ተረቱ ይሄ ስሕተት እንዳይፈጸም የሚያስጠነቅቅ ነው ማለት ነው፡፡ እናም ጠለቅ ብሎ ለመረመራቸው ያለ አንዳች እውነታና አገልግሎት የሚፈጠሩ ሥነቃሎች፣ ተረቶች፣ አባባሎች፣ ጥቅሶች እንደሌሉ መረዳት አይቸግረውም፡፡ የተረቶች ጥቅም ማስገንዘብ፣ ማስተማር፣ ማስጠንቀቅ፣ መረጃ መስጠት፣ ማፈላሰፍ፣ ታሪክን ማስጠበቅ፣ ትውፊትን ማስተላለፍ፣ ያጠፋን መገሰጽ፣ የታበየን ልኩን በመንገር ልኩን በማሳወቅ ማስታገስ፣ የደከመውን ማበርታት፣ ተስፋ የቆረጠውን በተስፋ መሙላት፣ የረዘመንና የተንዛዛን ነገር በአጭርና በተመጠነ ቃል በመግለጽ ጊዜንና መሰል ነገሮችን መቆጠብ፣ ለቋንቋ ውበትና ጥራት መስጠት፣ ንግግርን ማብሰል ወዘተ. ናቸው፡፡

እንጂ ለሕፃናት ዋጋና ቦታ ላለመስጠት ለመናቅ አይደለም፡፡ ወደ ገዳማት ብትሔዱ የማንም ልጅ ይሁን የማን የሦስት ዓመት ሕፃንም ቢሆን "አንቱ ወይም እርስዎ" ነው የሚባለው፡፡ በሌሎች ማኅበረሰቦች ብትሔዱ ይሄንን ዓይነት አክብሮት የምታገኙ አይመስለኝም፡፡ ሲጀመር "እርስዎ፣ እርሳቸው፣ አንቱ" የሚል የአክብሮት መግለጫ ቃል የላቸውም፡፡ አሁን እንግሊዝኛን ብንወስድ ሰር (የተከበሩ) በማለት ሰው ለማክበር ይሞክራሉ እንጅ "እርስዎ፣ እርሳቸው፣ አንቱ"

የሚባሉትን ቃል የሚተካ በዕድሜ ለገፉና ክብር ሊሰጣቸው ለተፈለገ ሰው አክብሮትን መግለጫ ቃል በቋንቋቸው ውስጥ የለም፡፡

ከዚሁ ከተረቶች ጋር በተያያዘ እነዚሁ ግለሰቦች ሐበሻን ሲያሙ የሐበሻ ባሕል መናገርን እራስን መግለጽን የሚያበረታታ አለመሆኑን ከተረቶቹ መረዳት ይቻላል ይሉና “ዝምታ ወርቅ ነው፣ ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባም እያለ ሰው እንዳይናገርና ሐሳቡን እንዳይገልጽ የመናገርና ሐሳብ የመግለጽ ክህሎቱን እንዳያዳብር ያደርጋል፡፡ ዝምተኛነትን ጨዋነት እንደሆነ አድርጎ ነው እንድናስብ የሚያደርገው” ሲሉ ይሰማሉ፡፡ እኔ እርግጠኛ ነኝ እነኝህ ሰዎች ሌላ ዓላማ ስላላቸው እንጅ ከላይ የጠቀሷቸውን ተረቶች እንደሰሙ ሁሉ “ካለመናገር ደጅ አዝማችነት ይቀራል!” በመናገር ሹመት ሽልማት የሚገኝ መሆኑን ጭምር በማመላከት መናገርን የሚያበረታታውን ተረት ሳይሰሙ ስለቀሩ አይመስለኝም፡፡ ሌላም የሚሉት አለ “ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል!” የሚለውን ተረት በመጥቀስ የሐበሻ አስተሳሰብ (mentality) መጨረሻ ይሄው ነው፡፡ ከዚህ አያልፍም ይላሉ፡፡ ይሄ የጠቀሱት ተረት እንዳለ ሁሉ ግን የዚህ ተቃራኒ የሆነና “ምድራዊው ነገር ሀላፊ ጠፊ ነው ለምድራዊውና ለጊዜአዊው ነገር ብለን ዘለዓለማዊውን አንጣ ግፍ በደል አንፈጽም” የሚል ምክርና ትምህርት ያዘለ ተረትም አለ “ከምድር ግሥ (ግሳንግስ) የሰማይ ውርስ፣ ከምድር ድቅ (ድቃቂ መናኛ ነገር) የሰማይ ጽድቅ” የሚሉና ግፍ በደል የፈጸመ ሰው የሥራውን የእጁን እንደማያጣ የሚስገነዝቡ “ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ካፉ፣ ስለት ድጉሱን ደባ ራሱን፣ በቆፈሩት ጉድጓድ ይገቡበታል፣ ሥራ ለሠሪው እሾህ ለአጣሪው” ወዘተረፈ. ደግሞ አሉ፡፡

ሁሉም ተረቶች በቦታቸውና በሰዓቱ ሲጠቀሱ ትክክልና አስተማሪም ናቸው ያለቦታቸው ሲገቡ ግን ውጤታቸው አሉታዊ መሆኑ አይቀርም፡፡ ምንም ነገር ቢሆን ያለቦታውና ያለሰዓቱ ሲገባ ነገር ማበላሸቱ ችግር መፍጠሩ አይቀርም፡፡ ለአሉታዊ ነገሮች ተረቶች እንዳሏቸው ሁሉ እነዚሁ በአሉታዊ መልኩ በተረት የተገለጹት ጉዳዮች እራሳቸው በሌላ ቦታ በአወንታዊ መልኩ ተረት ወይም ሥነ ቃል ወጥቶላቸው ታገኟቸዋላቹህ፡፡ ያንን ለአንዱ ጉዳይ በአሉታዊ የተነገረለትን ተረት በአወንታዊ ሰዓት ብትጠቀሙት ውጤቱም ሆነ አጠቃቀማቹህ የተሳሳተ በመሆኑ የተሳሳተ ግንዛቤንና መልእክትን ማስተላለፉ አይቀርም፡፡ በግልባጩ ስታደርጉትም እንደዚያው፡፡ ከዚህ አንጻር ተረቶችን ያለቦታቸውና ሰዓታቸው ከጠቀሷቸውና ከተጠቀሙባቸው ስሕተት መሆናቸው አይቀርም፡፡ ችግሩ ግን የተጠቃሚው እንጅ የተረቶቹ ወይም ተረቶቹን ፈጥሮ የሚጠቀምባቸው ኅብረተሰብ አይደለም፡፡ ስለሆንም ለእነኝህ ሰዎች ልነግራቸው የምፈልገው ነገር ቢኖር ተረቶቹ ሲጠቀሱ ያልገባቹህ ያልተረዳቹህት ነገር ካለ “ኧረ እኛ አልገባንም” በሉ እንጅ ሳይገባቹህ በተሳሳተ ግንዛቤ እየተረዳቹህ ለተረቶቹ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት የተረቶችን መልእክት አታዛቡ ዋጋቸውን አታራክሱ፡፡ ተርጉሙልን አስረዱን? ምን ማለት ነው? አልገባንም ብትሉ አትሞቱም ከእናቱ ሆድ ተምሮ የወጣ የለምና ጠይቆ መማርን እንደ እንከን አትዩት እንከኑስ ያልገባቹህን የማታውቁትን ነገር እየቀባጠራቹህ ሕዝብ ማሳሳታቹህ ነው፡፡

በሥነ ቃሎቻችን ውስጥ አጥቂና የማይመቹ ተረቶች አባባሎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል እነሱም ቢሆን የራሳቸው ዓላማና ጥቅሞች አላቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን የአንዳንድ ዋልጌዎችን አባባል እየጠቀሱ በእነሱ አባባል አንድን ማኅበረሰብ ተጠያቂ ማድረግ መውቀስ መኮነን ተገቢ አይደለም፡፡ እንደ ማኅበረሰብ ከመሀላችን ዋልጌዎች አይጠፉ ይሆናል ከዚህ የጸዳ ዋልጌ የሌለበት ማኅበረሰብም የለምና፡፡ እናም ከዚያ ማኅበረሰብ የሚበዛውን ቁጥር ያያዙት ዋልጌዎች እስካልሆኑ ጊዜ ድረስ እነሱ የማኅበረሰባችን አባል ናቸውና ተብሎ የእነሱ አባባል ማኅበረሰቡን ይወክላል ማለት በጣም የተሳሳተና ያልበሰለ አስተሳሰብ ነው፡፡ እኔ እንዲያውም ዋልጌዎች ሐሳባቸውን በሥነቃል መግለጽ በመቻላቸው የሚታየኝ ምንድን ነው? የእኛ ማኅበረሰብ ዋልጌዎች ከሌሎች ማኅበረሰቦች ዋልጌዎች ምን ያህል የበሰሉ የተሻሉ መሆናቸውንና ዋልጌዎቻችን እንኳ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ዋልጌዎች የላቁ የበሰሉ መሆናቸውን ነው፡፡ እናም ይህ ነገር በዚህ መልኩ ነው መታየት ያለበት፡፡

ሌላው መታሚያችን ደግሞ "ሐበሻ አያመሰግንም፣ አያደንቅም፣ የሚታየው ግማሽ ባዶው ነው እንጅ የፈለገ ቢሆን ግማሽ ሙሉ ነው አይልም" የሚለው ነው፡፡ እኔ ከየት እያመጡ እንደሚያወሩት አላውቅም፡፡ ይገርማቹሀል ይሄንን የሚሉት እኮ "When I am right no one remember, when I am wrong no one forget, ትክክል ስሆን ማንም አያስታውስም ስሳሳት ማንም አይረሳም" በሚሉትና እንዲህ ዓይነት ስር የሰደደ ያለመመስጋገን ችግራቸውን የሚገልጽ ሥነቃል ባላቸው ምዕራባዊያን መሀከል ሆነው ነው፡፡ እውነቴን ነው የምላቹህ ለማመስገንስ የሐበሻን ያህል አመስጋኝ ሕዝብ ጨርሶ የለም ብል በፍጹም ማጋነኔ አይደለም፡፡ ሐበሻ ትንሽ ነገር ስታደርጉለት ከማመስገንም አልፎ ምርቃትን የሚያዥጎደጉድ ሕዝብ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሕዝብ ከየት ታገኛላቹህ? እኔ እንግዲህ የማውቀውን ልናገር፡- ተወልጀ ያደኩት ጎንደር ከተማ ነው፡፡ ያው የሐበሻ ኑሮ እንደምታውቁት ዕቃ እየተዋዋሰ እየተበዳደረ ነው የሚኖረው፡፡ ልጆች ሆነን ቤተሰብ ከጎረቤት የተዋሰውን ዕቃ መልሱ ስንባል እንዲህ ብለህ መልስ ተብሎ የሚነገረን ቃል አለ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ ተባረኩ" የሚል፡፡ ይሄንን ብለን ዕቃውን ሰጥተን እንመለሳለን፡፡ ሌሎች ሀገራት ስንሔድ ግን ሲጀመር ዕቃ መዋዋስ የሚባል ነገር የለም ካለም በእኛ ደረጃ አይደለም፡፡ ሲቀጥል ቢበዛ አመሰግናለሁ ይባላል እንጅ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ማመስገን እንዲባርካቸውም መልካም ምኞት መመኘትና መመረቅ የለም፡፡

ወደ ገጠሩ ስትሔዱ ደግሞ በጣም የሚገርም ነገር ነው የሚገጥማቹህ፡፡ ገጠር ሰው ብቻ ሳይሆን በሬውም ላሚቱም ሳይቀሩ ይመሰገናሉ ያውም በዜማ፡፡ ከብቶች ግጦሽ ውለው ሲመለሱ እንደሰው "እንደምን ዋላቹህ ደኅና ዋላቹህ?" ተብለው ሰላምታ ይሰጣቸዋል፡፡ የገጠር ሰው ስላወቃቹህ ብቻ አይደለም ሰላምታ የሚሰጣቹህ አወቃቹህም አላወቃቹህ መንገድ ላይ ያገኘውን ሰው ሁሉ ነው የእግዚአብሔር ሰላምታን ሰጥቶ የሚያልፈው፡፡ ይሄ ባሕል ለማየት ዕድሉ ባጋጠመኝ በሌሎች የሀገራችን ክፍሎችም እንዳለ ዐይቻለሁ፡፡ በእርግጥ እኔ ምን እንደሆነ አላውቅም ከሕዝባችን ቁጥር 15 በመቶውን በሚይዘው በከተማ ሰው ላይ ግን ያለው ነገር ግን ከዚህ የተለያና ሐሜቱን እውነት የሚያስመስል ነው፡፡ እንኳንና እንደ

ገጠሩ ሰው እንደፈረንጅ እንኳን አመሰግናለሁ የሚለው በጣም ጥቂቱ ነው፡፡ ይመስለኛል ከተማ ከዚያም ከዚህም ከተለያየ ባሕል ሃይማኖት አስተሳሰብ መጥተን የምንጠራቀምበት የምንታጎርበት በመሆኑ ባለው የእርስ በእርስ መፈራራት መናናቅ መጠራጠር፣ የእኔ ካንተ እበልጣለሁ መታበይ፤ የለም እኔ ካንተ አላንስም ፉክክር ምክንያት ይመስለኛል ገጠር ላይ ያለንን ምስጉን ሥነ ምግባርና ግብረገብነት ከተማ ላይ በተለይም እንደ አዲስ አበባ ባለ የብዙ የተለያየ ዓይነት ማኅበረሰብ ባለበት ከተማ ላይ ለመፈጸም የምንቸገረው፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን በጥቅሉ ሲታይ አንድ የሆነ ዓይነት የሐበሻነት ቀለም አዲስ አበባ ላይ አለ፡፡

"ሐበሻ አያደንቅም ግማሽ ጎደሎው ነው የሚታየው የፈለገ ቢሆን ግማሽ ሙሉ ነው አይልም!" የሚለውን ሐሜት በሁለቱም አቅጣጫ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው እውነትነት እንዳለው አድርገን ስናየው፡- አዎ ሐበሻ አያደንቅም ካደነቀም በጣም በስሱ ነው፡፡ በደንብ ያለስስት ለማድነቅ ያ ሰው በዚያ በጎ ምግባሩ በምስጉን ሰብእናው መዝለቁን መጽናቱን ማረጋገጥ ይፈልጋል፡፡ የዚህም ምክንያቱ በሃይማኖታዊ አስተምህሮ በጎ ሥራ ሠርቶ መመስገን መወደስ ያ ሰው መልካም በመሥራቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያሰጠውን ዋጋ ያሳጣል የተከለከለም ነውና ነው ማቴ. 6፤1-5

በዚህ አስተምህሮ መቀረጽ የተነሣና እንዲሁም ደግሞ አድናቆት ተደናቂን ስለሚያስታብይ አስታብዮም ስለሚያሰናክል ስለሚያሳስት የሰው ልጅ አቅለ ቀላል ስለሆነ በትንሽ አድናቆት ታብዮ እራሱን እንደ ፈጣሪ በመቁጠር የማይገቡ ነገሮችን ሁሉ እስከማድረግ ይደርሳልና ከነዚህ ሁለት ምክንያቶች አንጻር ሐበሻ ልጆቹን ላለማጣት፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ላለማሳጣት፣ ከፈተና ለመጠበቅ ተሰናክለው ላለማየት አያደንቅም፡፡ ነገር ግን የሠሩት ሥራ ግሩም መሆኑን በተለየ የራሱ መንገድ አክብሮት በመስጠትና በመሳሰሉት ነገሮች አድናቆቱን ይገልጣል፡፡ አፉን አውጥቶ አድናቆቱን የሚሰጠው የሚያወድሰው የሚያከብረው ግን ያ ሰው በሞት በተለየ ጊዜ ነው፡፡ ያኔ ግን "አሁን ባደንቀው ውዳሴ ከንቱ ሆኖ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያሳጣዋል ታብዮም ይሰናከልብኛል" የሚል ሥጋት ስለማይኖረው የቆጠበውን ያህል ልክና ገደብ በሌለው አድናቆት በቅኔ ብትሉ በዜማ ያንን ሰው ያደንቃል ያመሰግናል ያወድሳል፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን ጎራ ብትሉ ይሄንን ታረጋግጣላቹህ፡፡ በሕይዎት እያሉ ከነመኖራቸው የማይታወቁ ቅዱሳን በኋላ ከሞቱ በኋላ ግን ገድላቸው ይጻፋል ሌሎች መታሰቢያዎችም እየተደረገላቸው እጅግ ይከበራሉ ይወደሳሉ ይደነቃሉ፡፡ እናም ሃይማኖታዊው አስተምህሮ ለባሕላችን መቀረጽ የአንበሳውን ድርሻ ስለሚይዝ ከዚህ የተነሣ ነው እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ሊኖረን የቻለው፡፡

"ሐበሻ አያደንቅም ግማሽ ጎደሎው ነው የሚታየው የፈለገ ቢሆን ግማሽ ሙሉ ነው አይልም" የሚለውን ሐሜት ሐሰት ብለን ከሌላኛው ጎን አንጻር ስናየው ደግሞ፡- በተቃራኒው ነው እየታማ ያለው ማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እንኳንና ግማሽ ድረስ ያለው ሆኖ ይቅርና ጥቂትም እንኳን ብትሆን እሷኑ ተመስገን ብሎ ተቀብሎ ሳያማርር የሚኖር

ማኅበረሰብ ነው ያለን፡፡ ምንም እንኳን ሙሉ ቢሆን የሚጠላ ባይሆንምና አጥብቆም የሚመኝ ቢሆንም ቅሉ ግማሽ ድረስ ያለው በመሆኑና ሙሉ ባለመሆኑ ካልሞላ አልፈልግም አልቀበልም የሚል አይደለም፡፡ ብዙዎቹ እንዲያውም ማኅበረሰባችንን እየነቀፉት እየተቹት ያሉት ዕቃው ጠብታም እንኳን ቢኖረው "ተመስገን ይህችን አታሳጣን" ባይነቱንና የበለጠውን የተሻለውን አጥብቆ ጠያቂ አለመሆኑን ነው፡፡ የሆነ ሆኖ እንደኔ አመለካከት ማኅበረሰባችን እንደሌሎቹ ማኅበረሰቦች እንዲህ ነው መገለጫው ይሄ ነው ተብሎ የሚገለጽ ሳይሆን እንደየ ዐውዱ በሁለቱም መገለጫዎች ሊገለጽ የሚችል የተለየ ቅኔ የሆነ ማኅበረሰብ ነው ብንል የሚሻል ይመስለኛል፡፡

ማኅበረሰባችን አንድ ሌላ የተለየ መገለጫም አለው፡፡ ማኅበረሰባችን አንድን ሰው ወይም የሆነ አካልን ሲከተልም አይቸኩልም ቀስ ብሎ ተረጋግቶ ጊዜ ወስዶ ዐይቶ አጥንቶ አጢኖ ጽናት እንዳለውና ታማኝ እንደሆነ፣ የሚናገረውን የሚለውን ነገር መሆኑን ኖሮት አድርጎት ማሳየቱን አረጋግጦ ነው መከተል የሚፈልገው፡፡ ትዕግስት ያስጨርሳል፡፡ ስሜቱ ወዲያው ቦግ ብሎ የሚጠፋ ሳይሆን ቀስ ብሎ የሚያያዝ የሚቀጣጠል ከተያያዘ ከተቀጣጣለ በኋላ ግን ቶሎ የማይጠፋ ነው፡፡ ና ስለተባለ አይመጣም ሒድ ስለተባለ አይሔድም፡፡ ተሰብስቦ ሳይወያይ ሳይማከር ልክ ተሰብስቦ እንደተማከረ ሁሉ በአንድ ነገር ላይ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ይዞ ታገኙታላቹህ፡፡ ልክ እንደ አንድ ሰው ነው የሚያስበው፡፡

እኔ ሕዝባችንን ሳስበው በጣም ነው የሚገርመኝ፡፡ እርግጥ ከሁኔታዎች ተለዋዋጭነትና ከውጫዊ አደናጋሪ ተጽዕኖዎች አንጻር ትክክለኛውን የኅብረተሰባችንን ልብ፣ አስተሳሰብ አግኝቸዋለው ማለት ቢከብድም በብዙ ነገር መርምሬዋለሁ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ከማንም የላቀ እጅግ ተደናቂ አስተሳሰብና መሠረታዊ ዘይቤ ያለው መሆኑን እንጅ የሚናቅና የሚጠላ ደካማ ማንነት ያለው መሆኑን አይደለም፡፡ አንድ ምሳሌ ልጥቀስላቹህ አሁን ሐበሻ እንደ ሐበሻነቱ ወያኔን የሚያህል ተውረኛና ቆሻሻ አገዛዝ የሚታገስ ሆኖ አልነበረም ይሄንን ያህል ዘመን መጫወቻ መቀለጃ አድርጎትም ጸጥ ብሎ የሚያየው፡፡ ነገር ግን ገና ከጅምሩ ወያኔ ፍጹም ኃላፊነት የጎደለው የማይሰማው ምንም ነገር ከማድረግ የማይመለስ አካል እንደሆነ ጠንቅቆ አውቆታል፡፡ ያም ሆኖ በዝምታው ውስጥ ባለ ቁጣና ዐመፅ ወያኔን እንዴት እንደሚያሸብረው እንደሚያስጨንቀው ዕያየን ነው፡፡ እስከ አሁን ባለው ጊዜ በወያኔ ላይ ያላመፀው ቢያምፅ ወያኔ ምን እስከማድረስ ሊደርስ እንደሚችል ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው፡፡

ስለሆነም ሁለት ያጣ መሆን አይፈልግም ሀገሩንም እራሱንም፡፡ ራሱን ሠውቶ ሀገሩን ማትረፍ የሚችልበትን አጋጣሚ ካጋጠመው ካገኘ ግን ራሱን ለመሠዋት ዐይኑን አያሽም፡፡ ውድ እናት ሀገሩን እራሱን እየሠዋ አቆይቷታልና፡፡ ወያኔም ይሄንን ስለሚያውቅ የሀገሩን ሕልውና መያዣ አደረገበት፡፡ ተቸገረ እንዴት ብሎ ያምፅ? ባመፀ ቅጽበት ሀገሩን እንደሚያፍራርስበት ስለሚዝትበት፡፡ ሽፍቶም እንዳይወጋው ይሄንን ማድረግ የሚችልበትን ዕድል የሀገሪቱን ብሔራዊ

ጥቅሞች ሳይቀር አሳልፎ በመስጠት ጎረቤት ሀገራትን በጥቅም በመያዝ መሸሻ መሸፈቻ አሳጣን፡፡ አማራጭ ጠፋ ምን ያድርግ? ምቹ አጋጣሚን አግኝቶ ሀገሩን እስኪያፈርስበት ጊዜ ድረስ ጊዜ ሳይሰጥ ድንገት በማመፅ ወያኔን በመቅደም ተቅሎ የሚጥልበትን አጋጣሚ ከመጠባበቅ በስተቀር ምንም ሊያደርግ አልቻለም፡፡ ሐበሻ የስሜት ብስለቱ ጥልቀቱ ርቀቱ አስተሳሰቡ እጅግ እጅግ እጅግ  የጠለቀ የመጠቀ ነው፡፡ በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ያለ የተማረ የተባለ ሕዝብ ነው የሚባል ማኅበረሰብ ብታመጡ ከጫፉ አይደርስም፡፡

ላው "ሐበሻ ሰው ሲሞት መቅበር ነው እንጅ በቁም መረዳዳት አያውቅም!" የሚለው ነው፡- ይሄም ፍረጃ እንደሌሎቹ ሁሉ የተሳሳተ ነው፡፡ በአስተውሎት ላላየውና ግልብ ለሆነ ሰው እውነት ይመስላል፡፡ ምሥጢሩ ግን ወዲህ ነው፡፡ አዎ! እንደምናየው ሐበሻ ሰው ሞተ ከተባለ ከቀብር ጀምሮ ኃዘንተኞች ኃዘናቸውን እስኪረሱ ማስተዛዘን ድረስ ሞቅ ባለ ርብርብ ያደርጋል፡፡ ብዙ ሰዎች "ሐበሻ ይሄንን ርብርብና መረዳዳት በቁም ቢያደርገው የት በደረሰ!" እያሉ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ ስላልገባቸው ነው፡፡ ሐበሻ በቁም መረዳዳት መደጋገፍ ጠቃሚና መሆን ያለበት መሆኑን አጥቶት አልነበረም ሰው ሲሞትበት በመረረ ቁጭትና ኃዘን ሸኝት የሚያደርግለት፡፡

ነገር ግን ከማጣት ከድህነት ጋር በተያያዘ የአቅም ውስንነት ቀፍድዶ ይዞት ለወገኑ ማድረግ ያለበትን ሁሉ ሳያደርግለት ከዛሬ ነገ ሞልቶልኝ እረዳዋለሁ እረዳታለሁ፣ እደግፈዋለሁ እደግፋታለሁ፣ ላደርግለት የምፈልገውን አደርግለታለሁ አደርግላታለሁ ብሎ እያሰበ እንዳለ ድንገት ያ ሰው ከጎኑ ሲለይ "ወይኔ ጌታዬ! ሞልቶልኝ ተሳክቶልኝ አንድ ነገር ሳላደርግለት ሳላደርግላት አመለጠኝ! አመለጠችኝ! ማለት ነው?" የሚለው ሊያምነው በማይፈልገው ነገር ግን በሚገደደው የኃዘን ቁጭትና ይሄንንም ቁጭት ለመግለጽና ጸጸት ለመቀነስ ያህል ነው ሐበሻ በለቅሶ ጊዜ የሚታየውን ያህል ተንገብግቦ እንዲረባረብ የሚያደርገው፡፡

እንጅማ ሐበሻ ትንሽ ያገኘ ያለው እንደሆን ሰበብ እየፈለገ ምክንያት እየፈጠረ ማኅበር፣ ዝክር ወይም ጸበል፣ ክርስትና፣ ተዝካር፣ ግብረሰላም ወዘተረፈ.. እያለ ደግሶ ማብላት ማጠጣት መጋበዝ በእግዚአብሔር፣ በቅዱሳን፣ በጻድቃን፣ በመላእክት ስም እንዳቅሙ ችግረኛን መርዳት አይደለም እንዴ ወጉ ባሕሉ ልማዱ? የድሀ ወገኑን ልጅ የድሀ ወገኑን ብቻ ሳይሆን ወገኑ ዘመዱ ያልሆነውንም በማደጎ ወስዶ ማሳደግ ማስተማር አቅሙ ደካማ የሆነበት ደግሞ ለድኃ ወገኑ ዱቄት ሳይቀር እየተሰጣጣ መደጋገፍ አይደለም እንዴ ልማዱ? የአንዱ ቤት ዕቃ ለሌሎች በመዋዋስ ሌላውንም እንዲያገለግል ማድረግ አይደለም እንዴ ባሕሉ? ይሄ ባሕል በሌላ በማን አለ? እናም ማጣት ይዞት እንጅ ሲኖረው እማ መረዳዳት መደጋገፉን ማን እንደ ሐበሻ የሚያውቅበት ነበረ? ይሄ ሕዝብ ነው ታዲያ በቁም ባለመረዳዳት ባለመደጋገፍ ሊታማ የሚገባው?

እንዲያውም ካላቹህስ ብቻውን በር ዘግቶ መብላት የመጣው አሁን አሁን የራሱን ንቆ ትቶ የምዕራባውያኑን ባሕል በሚከተለው ተማርኩ ሠለጠንኩ በሚለው የማኅበረሰባችን ክፍል ዘንድ ነው እንጅ የእኛማ ባሕል አብሮ በመብላት በመደጋገፍ በመረዳዳት ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ የሚገርማቹህ እንዲህ እያሉ ያለሥራው ሳይገባቸውና ሳያውቁት የሚያሙት ሰዎች መልሰው ደግሞ ዞር ይሉና ይሄንን የማብላት የማጠጣት የመደጋገፍ ባሕሉት ካለመሠልጠን፣ ካለመማር፣ ብልጥ ካለመሆን፣ የቁጠባ ባሕል ካለመያዝ፣ የገንዘብን ጥቅም ካለመረዳት የያዘው የአባካኝነት ባሕል እንደሆነ በመናገር ሲኮንኑት ደግሞ ታገኟቸዋላቹህ፡፡ ለመንቀፍ ለመኮነን ብቻ የተዘጋጁ ስለሆኑ ጭንቅላታቸው ነገሮችን በእኩልና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚገመግምበት የሚፈትሽበት የሚዳኝበት ሚዛንና አመክንዮ የሚባል ነገር የለውም፡፡ እሴቱ ሲኖረውም ሳይኖረውም ይኮንኑታል ያሙታል ያጣጥሉታል፡፡ አይገርምም?

ሌላው "ሐበሻ ለሴት ልጅ ክብር የለውም! መብቷንም አይጠብቅም ሴት በመሆኗ ብቻ በሴት ላይ ጥቃት የሚፈጽም ማኅበረሰብ ነው" ይገባኛል ይሄንን ብየ ስል ብዙ ባለ አእምሮ ወገኖች በደናቁርቱ ፍጹም የተሳሳተ አባባል በእጅጉ ልባቹህ እንደሚደማ እንገዲህ ምን ይደረግ እነሱ አሉታ ባይሆን ከእኛ የሚጠበቀው ተገቢውን መልስ በመስጠት ድንቁርናቸውን ማጋለጥና በግልብ አባባላቸው እንዲያፍሩ እንዲሸማቀቁ ማድረግ ነው፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ማለት የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር እኔ በግሌ "የሴቶች ጉዳይ ወይም የሴቶች ምንትስ" የሚባሉ ሥያሜዎች ሁሉ አይመቹኝም፡፡ ምክንያቱም ሴቶችን የሚያጠቁ ወይም የሚበድሉ ባሎች ወይም የወንድ ጓደኞች ወይም ወንድሞችን ስናይ ሴቶቻቸውን የሚያጠቋቸው ሴት ስለሆኑ ወይም ወንድ ስላልሆኑ አይደለምና፡፡ ሴት ስለሆነች ወይም ወንድ ስላልሆነች ብቻ ጥቃት የሚያደርስ ሰው ካለ እስካሁን ሰምቼ አላውቅም ይኖራል ብዬም አልገምትም አለ ከተባለ ግን ይህ ሰው ጤነኛ ባለመሆኑና ይህ ለየት ያለ (Exceptional) በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በተለየ ሁኔታና ቦታ እንበል ለምሳሌ በአእምሮ ሕሙማን ማዕከላት ዓይነት ቦታ ነው፡፡

ጉዳዩ ወይም ችግሩ ግን ፈጽሞ የማኅበረሰቡ ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ ይህንን ካደረግን ግን ማኅበረሰቡን መስደብና ማዋረዳችን ነው፡፡ በደል የተፈጸመባቸውን ሴቶች የበደል ዓይነቶች ያየን እንደሆነ እነዚያ የተፈጸሙ በደሎች ሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ በወንዶችም ላይ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ በመሆኑም በደሉ የተፈጸመባት ሴት ያ በደል የተፈጸመባት ሴት በመሆኗ አይደለም ማለት ነው፡፡ ታዲያ ምንድነው? ያልን እንደሆነ በጉልበትና በመሳሰሉት ነገሮች በደል ከሚያደርሰው ሰው ያነሰች ስለሆነች ነዋ! በማነሷም በጉልበት ከእሱ ማነሷን ምቹ አጋጣሚ ተጠቅሞ ከእሷ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት ወይም ለመበዝበዝ ነው፡፡ ወንዶች ያላቸውን ጉልበት የሴቶች ሴቶች ያላቸውን የጉልበት ወይም የአቅም ውሱንነት ለወንዶች አድርገን ብናስበው ይህ አሁን በሴቶች ላይ እየተፈጸመ ያለው ችግር ሁሉ የሚታሰብ ባልሆነም ነበር፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የጉልበተኞች እና የአቅመ ውስኖች ጉዳይ እንጂ በፍጹም የጾታ ጉዳይ ወይም ሴት እና ወንድ የመሆን ጉዳይ አይደለም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በወንዶችም ላይ የሚፈጸመው ይሄው ነውና፡፡ ጉልበተኛው አቅመ ቢሱን ወይም ደከም ያለውን ሲጎዳው ሲያጠቃው ሲበድለው ሲበዘብዘው እንደሚታየው ሁሉ ማለት ነው፡፡ ሕፃናት ወንዶች ለመግለጽ የሚቀፍ ማለትም የወሲብ ጥቃት ሰለባ በሆኑበት ሁኔታ የጥቃት ዓይነቶችን በፆታ ወስነን እንዴት ነው "የሴቶች ምንትስ" ልንል የምንችለው? ፆታ የለየ ጥቃት ከሌለስ እንዴት ነው ጥቃትንና ፆታን ልናያይዝ የምንችለው?

በዚህም ምክንያት "የሴቶች ምንትስ፣ የሴቶች እንደዚህ፣ አሁንም የሴቶች ቅብርጥስ" የሚባሉ ነገሮች ሁሉ ችግሩንና ጉዳዩን በትክክል ማየት መግለጽ መወከል ካለመቻላቸው የተነሣ ሥያሜዎቹ ፈጽሞ አይመቹኝም፡፡ ይሄ እንዲያውም የፖለቲከኞች ቁማር ይመስለኛል፡፡ ማኅበረሰባቸውን በተገቢው መንገድ ማስተዳደር ሲያቅታቸው ወይም ከማኅበረሰቡ ለሚሰነዘሩ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ሲሳናቸው የማኅበረሰቡን ትኩረት ማስቀየሻ እና ከእነሱ ላይ ዞር ማድረጊያ ለዚያ ማኅበረሰብ እዚያው ባለበት የሚይዙላቸውን ፆታን እና የመሳሰሉትን ርእሰ ጉዳዮች መሠረት ያደረጉ  የተለያዩ የልዩነት የቤት ሥራዎችን ሆን ብለው ይፈጥራሉ፡፡ ይሄም እንግዲህ ከቤት ሥራዎቹ አንዱ መሆኑ ነው፡፡

ህን ስል ግን ለተገፉ ወይም ለተጠቁ ሰዎች ጥብቅና አይቆም ይረሱ ይገለሉ ማለቴ እንዳልሆነ መረዳት የሚችል ጭንቅላት ያለው ሰው ሁሉ ይረዳኛል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ነገር ግን ዓላማችን የተገፉትን ወይም የተጠቁትን ሰዎች ሙብት ማስከበር ወይም ማስጠበቅ ከሆነ አቅምን አይቶ ወይም ገምቶ በአቅም ውስንነት ምክንያትም በተወሰኑ የማኅበረሰብ ክፍል ላይ ብቻ አትኩሮ መሥራት ካስፈለገ ወይም ግድ ካለ በተሳሳተ ሚዛን ጾታን መሠረት ባደረገ ሥያሜ በጅምላ "የሴቶች ሙብት" በማለት ሳይሆን "የተጠቂ ሴቶች ጉዳይ" ወይም "የግፉአን ሴቶች" ማለትም "የተገፉ ሴቶች ሙብት ተከራካሪ ወይም አስጠባቂ" ቢባል ትክክለኛ ሥያሜ ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም የማይጠቁና ያልተጠቁ ሴቶች አሉና፣ ያልተገፉና የማይገፉ ሴቶች አሉና፣ የተከበሩ እና የሚከበሩ ሴቶች አሉና፣ ያልተደፈሩና የማይደፈሩ ሴቶች አሉና አብሶ ለእኛ ለሐበሾች ይሄ ሊነገረንና በዚህ ልንታማ ጨርሶ የሚገባ ጉዳይ አልነበረም፡፡ ከተሞከረም ድፍረት ነው፡፡

ማንም ነጭ ለእኛ ለሐበሾች አፍ አለኝ ብሎ እና ደፍሮ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ሐበሻን እንደ ሐበሻ ሊነቅፍ ወይም ሊኮንን የሚችልበት አንድም የሞራል (የቅስም) እና የመንፈስ ብቃት አቅምና ነፃነት ከቶውንም አይኖረው፡፡ በታሪኩ የሴት መሪ አይቶ ወይም አግኝቶ አብቅቶ የማያውቅ ድኩም ኅብረተሰብ ከቀዳማዊት ሳባ (ከዛሬ 4380-4370 ለ 10 ዓመታት የነገሡች) ጀምሮ እስከ ዘውዲቱ ከ ሃያ በላይ ገናና ብልህ አስተዋይ ብቁ ጀግና ቆራጥ ሴቶችን ያፈራንና ያበቃን ሕዝብ እና ሀገር "ሴቶችን ምንትስ…" እያለ ሐበሻን ሊነቅፍ ሊመክር ሊኮንን ሊተች የሚችልበት ኧረ በየትኛው ሒሳብ ይሆን?

እንደ አለመታደል ሆኖ በዚህ ዘመን ካለን ሐበሾች ጥቂት የማንባለው አፈር ያብላንና ለነገሩ በልተናል ከዚህ በላይ አፈር መብላት የት አለና፡፡ እናም ክብራችንን ዋጋችንን (ቫሊዩአችንን) ባለማወቅ የዚያ ችግር ባለቤት ወይም ተጠቂ የሆኑ የበርካታ ምዕራባዊያን ሀገሮች ጩኸት ሴቶችን ለመሪነት ማብቃት አይደለም ለሴቶች እንደ ሰው የሰውነት መብት ከሰጡ እንኳን ከአንድ የእድሜ ባለጸጋ አረጋዊ እድሜ የማያልፉትን፣ የሴቶችን ሰብአዊ መብቶች በተጻፉ ሕጎቻቸው ሳይቀር በይፋ የደፈለቁትን ኅብረተሰቦች ወይም ሀገሮች ጩኸት የሴቶችና የወንዶች የሚል ልዩነት ሳታደርግ እስከ የመጨረሻው የሥልጣን ደረጃ አብቅታ ባረጋገጠች ሀገር፣ በሐበሻ ባሕል ሴት ልጅ የክብር ምልክትና መገለጫ ናትና ክብሯን ለመጠበቅ ታስቦ ካልሆነ በቀር ጾታዋን እንደበደል በመቁጠር በማኅበራዊ ሕይዎት ላይ ምንም ዓይነት ገደብ አድርጎ በማያውቅ ኅብረተሰብና ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ በእኛው በሐበሾች አፍ ስንጮኸው ጉዳዩ ምን ያህል አሳዛኝና ልብ የሚሠብር እንደሆነና በዚህ ዘመን ያለነውን ሐበሾች ያለንበትን የሞራል (የንቃተ ወኔ) ዝለት፣ ኪሳራና ዝቅጠት የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ ምንአልባት አንዳንድ የሚመስሉና የሚታዩ ነገሮች ካሉም ወይም ቢኖሩም እነኚህ ጉዳዮች ድህነታችን የፈጠራቸው ሳንኮች እንጂ በፍጹም እንደ ሐበሻ በሴት ልጅ ላይ የተዛባና የተሳሳተ አስተሳሰብ ኖሮን ይሄንንም የባሕላችን አካል ወይም የአስተሳሰባችን ደረጃ አድርገነው አይደለም፡፡

ሌላው ደግሞ "ሐበሻ ሃይማኖተኛ እየተባለ የሚገለጸው ውሸት ነው! በባዕድ አምልኮና በጣኦት አምልኮ የተተበተበ ሕዝብ ነው!" የሚለው ነው፡፡ ይሄንን አባባል ሰባኪያን ነን ባዮች ሳይቀር በየገድላቱ ያለውን "የዚህ አካባቢ ሕዝብ አባ እክሌ ሰብከውት ከማሳመናቸው በፊት በዘንዶ ያመልክ ነበረ፣ ከምልኮ እግዚአብሔር ርቆ ነበር" የሚለውን ቃል እየጠቀሱ እግዚአብሔርን አምላኪነቱ ውሸት ነው በማለት ያነሡታል፡፡ እርግጥ ነው እንዲህ ዓይነቱ ችግር በዚያ ዘመን ነበር እነኝህ ግለሰቦች ልብ ያላሉት ነገር ሰይጣን እስካለ ጊዜ ድረስ እንዲህ ዓይነቱን ችግር ማጥፋት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ይህ ችግር እንኳን በዚያ ዘመን ዛሬም ድረስ ያለ ነው ወደፊትም ይኖራል፡፡ ይሄ ግን እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ሕዝብ አለመመለኩን ወይም ኢትዮጵያ ከሕገ ልቡና ጀምራ የነበራትንና ያላትን ቁርኝት የሚያስተኃቅር ወይም የሚያስተባብል አይሆንም፡፡

ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ልብ ሊሉት የሚገባው ነገር ቢኖር እስራኤላዊያን እራሳቸው ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር በገሀድ በተጨባጭ በግልጽ ስንት ተአምራትን እያደረገላቸው እያለ እዛው ላይ ዞር እያሉ ለጣዖት ያልሰገዱበት ከጣኦት አምልኮ የራቁበት የተለዩበት ዘመን ኖሮ አያውቅምና፡፡ በእግዚአብሔር ወኪሎች በነቢያቱ የቅርብ የትምህርትና የተግሳጽ ክትትል ስር የሆኑት ነገሥታቶቻቸው ሳይቀሩ ከንጉሥ ዳዊትና ከኢዮስያስ በስተቀር ለጣኦት ያልሰገደ ንጉሥ ኖሯቸው አያውቅም ነበርና፡፡ ስለሆነም እግዚአብሔር በግልጽ መታወቁና መታመኑ በራሱ ብቻውን እስራኤላዊያን ፊታቸውን ወደ ጣዖት አምልኮም ሆነ ወደ ባዕድ አምልኮ እንዳያዞሩ ወይም እንዳይከተሉ ሊያደርጋቸው እንዳልቻለ ሁሉ እኛም ከሰው

የተለየን አይደለንምና በእኛም ዘንድ ያለውና የነበረው ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ እንደ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ እግዚአብሔር በሰው ልጆች በተመለከና በከበረ ቁጥር ሰይጣን እየቀና የዛኑ ያህል እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከአምልኮተ እግዚአብሔር ለማሸሽ ለመለየት በአገልጋዮቹ በጠንቋዮችና በቃልቾች እያደረ አንዳንድ ተአምራትንም እያሳየ እያደረገ ባዕድ አምልኮን እንዲሁም በኤር. 6፤16 በኤፌ.4፤5 በዕብ. 3፤14 በይሁ. 1፤3 ላይ ከተጠቀሰችው አንዲቷና ብቸኛዋ ሃይማኖት ውጭ ሌላ ተመሳሳይ ሐሰተኛ ሃይማኖት መሰል ድርጅቶችን እየሰበከ አማኞችን ከሃይማኖት ያስወጣል ያስክዳል፡፡ ይሄንንም ያለማሰለስ ሲሠራ ኖሯል ይኖራልም፡፡ ሌላ ሥራ የለውም ሥራው ይሄ ብቻ ነው "መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው" 1 ኛ ጢሞ. 4፤1 እናም ያለው ነገር ይሄው ነው ከዚህ ውጭ ምንም አዲስ ነገር የለም፡፡

እንግዲህ ለማስያዝ የፈለኩት ጭብጥ "አየ ሐበሻ!'' ብለን ቃል ከማውጣታችን በፊት ይህ ነውር ወይም ችግር የሚፈጸመው በሐበሻ ብቻ ነው ወይ? ካልሆነስ እኛ እንሻላለን ወይንስ እንብሳለን? በማለት እራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል ይሄን ብለን መጠየቃችን እንደ አንዳንድ ግልብ ደራሲዎቻችንና ታዋቂ ሰዎቻችን የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዳንደርስና በማንነታችን በሰብእናችን ላይ ቋሚ ጉዳት እንዳናደርስ ሌላውንም እንዳናሳስት ወይም እንዳናደናግር ይታደገናል፡፡

በቅርቡ ነው አንድ የተማረ ሰው ነው የተባለ የተነገረው ነገር ምን ያህል እውነታነት አለው ብሎ አቅሙ የቻለውን እንኳን ያህል ሳይመረምር የሐበሻን ቅስም ለመስበር ሆን ብለው ከሚያሴሩ አካላት የተወረወረውን እንዳለ ተቀብሎ በመዋጥ መልሶ ለዛውም በብዙኃን መገናኛ ለሕዝብ ሲተፋው እጅግ ነበር የበገንኩት ከሱ እየተቀበሉም ሌሎቹ ናኘተውታል ወሬው፡- "ወሲብ ነክ የሆኑ የመካነ ድር ገጾችን በመጎብኘት ሀገራችን ከዓለም ሀገራት ቀዳሚ ናት" የሚል ነው፡፡ ይህ ሰው አስተዋይ ቢሆን ኖሮ ማንንም መጠየቅና መቸገር ሳያስፈልገው የዚህን የጠላት ወሬ ሐሰተኝነት በቀላሉ ሊያረጋግጥ በቻለ ነበር፡፡

በሀገራችን የመካነ ድር (የኢንተርኔት) ተደራሽነት ከአንድ በመቶ በላይ አይደለም፡፡ እሱም ቢሆን እንደሌሎች ሀገራት የተቀላጠፈ የድረገጽ አገልግሎት የሚሰጡ የመካነድር ወይም የድረገጽ መጠቀሚያዎች (internet café) ስለሌሉ አጠቃቀሙ በአብዛኛው በመሥሪያ ቤቶች እጅ ያለ ነው፡፡ ይሄም ማለት ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንጻር መካነ ድር የመጠቀም ዕድል ያለው ሰው እጅግ በጣም ኢምንት ነው ማለት ነው፡፡ የሌሎች ሀገራትን በተለይ የምዕራባዊያን ሀገራትን የመካነድር አጠቃቀምና ሽፋን ያየን እንደሆን መካነ ድር የመጠቀም ዕድል የሌለው ዜጋና የድረ ገጽ አገልግሎት ተደራሽ ያልሆነበት ቦታ የላቸውም፡፡ አቅርቦቱና ዕድሉ ለሁሉም ለእያንዳንዱ ዜጋ ክፍትና ተደራሽ ነው፡፡ አይደለም በምእራቡ ዓለም እዚሁ ከምሥራቅ አፍሪካ ጋር ያለን የአገልግሎት ሒሳብና የተደራሽነት ልዩነት የሰማይና የመሬት ያክል ነው፡፡

እንግዲህ እውነታው እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ነው ሀገራችን ወይም ሕዝባችን ወሲባዊ የመካነ ድር ገጾችን በመጎብኘት ከእነዚህ የመካነ ድር ሽፋን ለሁሉም ሕዝባቸው ከተዳረሰበት የምዕራቡ ሀገራትም አልፋ ቀዳሚ ሆነች እያሉን ያሉት፡፡ እንዲያው በዚህ ከአንድ በመቶ የማይበልጥ መካነ ድር የመጎብኘት ዕድል ያላቸው በመሥሪያ ቤትም በምንም ያሉ ሠራተኞች ሁሉ ሥራቸውን ትተው በየተራ እንደዚያ ዓይነት ወሲባዊ ትዕይንቶችን የሚያሳዩ መካነ ድሮችን ወይም ድረ ገጾችን ይጎበኛሉ ቢባል እንኳን በምዕራባዊያን ሀገራት ከሁለትና ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች እነዚያን የመካነ ድረ ገጾች የሚጎበኙትን የሚያህል ሊሆን እንደማይችል መረዳት እጅግ ቀላል ይመስለኛል፡፡ በምዕራቡ የዓለማችን ክፍል በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (Colleges and Universities) ላይ ያሉ ተማሪዎቻቸው እነዚህ ዓይነቶችን ድረ ገጾች በመጎብኘት በከፍተኛ ተጠቃሚነታቸው ይታወቃሉ ይህ ጉዳይም ለየየትምህርት ተቋማቶቻቸው ብሎም ለየሀገሮቻቸው የራስ ምታት እንደሆነባቸው ይታወቃልና፡፡ እናም በቀላሉ ይህ ወሬ ጠላት ሆን ብሎ የሀገራችንንና የሕዝባችንን ስም ለማጠልሸት የፈጠረው ሰይጣናዊ ስም ማጥፋት ሆኖ እናገኘዋለን ማለት ነው፡፡ እናም እባካቹህ ሰዎቻችን ሆይ! ዝም ብላቹህ የጋቿቹህን ሁሉ እንዳለ እየዋጣቹህ መልሳቹህ አትትፉብን መርምሩ፡፡ እውነት ነው ወይስ አይደለም? ዓላማውስ ምንድን ነው? ብላቹህ ለማጤን ትንሽም እንኳን ሞክሩ፡፡

ሐበሻን ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋራ ስናነጻጽር ሀገራችን ያላትን የምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚ) አቅም፣ አሁን ያለውን የማኅበረሰባችንን ንቃተ ኅሊናና የዕውቀት ደረጃ ባጠቃላይ ያለውንና የነበረውንም ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሄ ሳይሆን ግን ዝም ብልን ተነሥተን የሀገራችንን ከተሞች ከአውሮፓ ከተሞች ጋር ብናነጻጽርና ብንነቅፍ አለመብሰላችንን ከሚያመላክት በስተቀር ሌላ የሚሰጠው ትርጉምም ሆነ ትምህርት አይኖርም፡፡ እንዲሁም የሕዝባችንን የጤናና የንጽሕና አያያዝና አጠባበቅ እያነሣን ከአውሮፓውያን ወይም ከአሜሪካዊያን ጋር ለማነጻጸርና ለመንቀፍ ብንሞክር አሁንም አግባብነት ያለው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ የመሠልጠንና ያለመሠልጠን፣ የማወቅና ያለመማወቅ፣ የመማርና ያለመማር ባጠቃላይ ዘመንን ተከትሎ የንቃተ ሕሊና የማደግና ያለማደግ ጉዳይ በመሆኑና ከእነሱ የቀደመው ሥልጣኔያችንና የሀብት አቅማችን ቀደም ሲል ባነሣናቸው ምክንያቶች ጠፍቶ ከዜሮ እንድንጀምር ስለተገደድንና በነዚያ ችግሮች ከአዋቂነት ወደ አላዋቂነት ከሀብታምነት ወደ ድሀነት ከሥልጡንነት ወደ ኋላቀርነት ስለተለወጥን ከዚሁ ጋር በተያያዘ ችግር የተፈጠሩ ማኅበራዊ ችግሮች ስለሆኑ፡፡

አውሮፓውያኑንም ዘመናዊ ሥልጣኔ ከመጀመራቸው በፊት ቀደም ቆየት ያለውን የሕይዎት ተሞክሯቸውን ብንመለከት ገና ዘመናዊነቱን አዲሱን ሥልጣኔ አልጀመሩም ነበርና ንቃተ ሕሊናቸው ገና አላደገም ነበርና የንጽሕናና የጤና አጠባበቅ ዘዴዎቻቸው ከእኛ ደካማ ተሞክሮዎች ወይም እኛ ከምንተችበት ምንም የተለየ አልነበረም፡፡ ያኔ እነሱም ሽንት

ቤት አያውቁም ነበርና መንገድ ላይ ይጸዳዱ ነበር፣ ገላቸው በክቶ ወይም ቆሸሾም ቶሎ ቶሎ መታጠብ "ነውርና ሴታሴትነት ነው" ብለው ያስቡ ስለነበር ወንዶቻቸው ቀርንተውም የሚታጠቡ አልነበሩም፡፡

በዚህ ደካማ የንጽሕና አጠባበቅ ችግራቸው የተነሣ የአንደኛው የአውሮፓ ሀገር ዜጎች የሌላኛውን "…ናቸው" እያለ የሚነቅፍበት የሚተችበት ስም የሚያወጣበት ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ በዚህ ችግር ምክንያት በተደጋጋሚ ለተለያየ ዓይነት ወረርሽኝ የተዳረጉባቸው አጋጣሚዎች በርካቶች ናቸው፡፡ ከእነኝህ ችግሮች እየተማሩና የምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚ) አቅማቸው ዕድገት በፈቀደላቸው መጠን ኑሯቸውን እያሻሻሉ እያዘመኑ እየተማሩ እየሠለጠኑ በመምጣታቸው አሁን ላሉበት የሠለጠነ የኑሮ ዘይቤ ደረጃ ሊደርሱ ቻሉ እንጅ ብዙዎቻችን እንደሚመስለን ከቀድሞውም ወይም ሲፈጠሩም እንደዚህ ስለነበሩ አይደለም፡፡ ዛሬ ግን የእነሱ ዘመናዊ የሕይዎት ተሞክሮ ለተቀረው ዓለም የደረጃ መለኪያ ለመሆን በቃ፡፡

አንድ መኪና አይቶ የማያውቅ ወይም ስለ መኪና ግንዛቤው የሌለው የገጠር ሰው ከአውቶቡሱ ኋላ ኋላ የምትሔደውን ሚኒባስ ዕያየ "አንተ! ይህች እንቦሳ ገና በልጅነቷ እንደዚህ የሮጠች እናቷን ስታክልማ ነፋስ መሆኗም አይደል!" ማለቱ ምን ደንቆሮ ነው አያሰኘውም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ የመማርና ያለመማር የማወቅና ያለማወቅ እንጅ የተፈጥሮ ባለመሆኑ፡፡ ያለማወቅ ወይም ያለመማር ችግር ደግሞ መበማር የሚፈታ በመሆኑ፡፡ አንዴ ኪነብጀታ (ቴክኖሎጂ) ጅማሮው ላይ የነበረውን ሁኔታ የሚያሳይ ዘጋቢ ምትርኢት (ዶኩሜንተሪ ፊልም) ሳይ ምን ዐየሁ መሰላቹህ ብዙዎቻቹህም ዐይታቹህት እንደሚሆን እገምታለሁ ምትርኢቱ ብስክሌት (እሽኩሊሊት) የፈጠረው ሰው የፈጠረውን እሽኩልሊት መንገድ ላይ ሲሞክር ያሳያል፡፡ በዚያ መንገድ ላይ የነበሩ አውሮፓውያን ይህ ሰው ብስክሌቱ ላይ ሆኖ ሲጋልብ ሲያዩ ምኑ መጣብን ብለው ደንብረው ሲፈረጥጡ ግማሹ በየጥሻው ግማሹ እግራቸው ወደ መራቸው ነፍሴ አውጪኝ ብለው ሲደነብሩ ያሳያል፡፡ ያኔ የሳኩትን ሳቅ መቸም ቢሆን አልረሳውም፡፡ በሌሎቹም በወቅቱ አዲስ ለነበሩ የኪነብጀታ (የቴክኖሎጂ) ውጤቶች ሁሉ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ነበር የታዩት፡፡

ምንም እንኳን ዛሬ ያንን በማድረጋቸው የሚያፍሩና የሚጸጸቱ ቢሆኑም ራቅ ወዳለው ዘመናቸው ስንሔድም በተለያዩ ባሕላዊ እምነት መሪዎቻቸው ፊታውራሪነት የተለየ ተራማጅ አስተሳሰብ ያፈለቁ ጥበበኞቻቸውንና ፈላስፎቻቸውን የሰይጣን አስተሳሰብ እያሉ በድንጋይ ወግረው የገደሉበት ዘመንም ነበር፡፡ እናም በኛም ላይ ያለው ሁሉ አዲስ ነገር አይደለም ዛሬ ላይ ያለው ትውልዳቸው ባያውቀውም እነሱ ያለፉበት ነው፡፡ እነሱ እየሠለጠኑ እያወቁ ሀብታም እየሆኑ ሲሔዱ እየተለወጡ እንደመጡ ሁሉ እኛም እየሠለጠንን እያወቅን ሀብታም እየሆንን ስንሔድ የምንለውጠው ነገር ነው፡፡ በዚህ መልኩ ብንረዳው መልካም ነው፡፡ ይሄው ነው በተረፈ ባጠፋሁኝ ይቅርታ የተሳሳትኩት ካለም እታረማለሁ እንዲያው ዝም ብለን አፋችን እንዳመጣልን ከምንናገር እያሰብን እያጤንን ቢሆንስ ለማለት ነው፡፡ ባይሆን እንዲህ እናድርግ "አየ ሐበሻ!"

ከምንል “አየ የሰው ልጅ!” ወይም እንደ አያቴ “አየ ሁለት እግር!” ብንልስ? ይሄም ሆኖ አሁንም እንዳንሳሳት ያንን ጥፋት የሠራውን ሰው ማለታችን እንጅ ባጠቃላይ የሰው ልጆችን ማለታችን እንዳሆነ ልብ ይሏል፡፡

ልዑል እግዚአብሔር የሀገራችንንና የሕዝባችንን ልዕልና ሞገስ ክብር ጸጋና በረከት ይመልስልን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com